# በ*ብሌን* (1982) የ*ፍቅር እስከ መቃብር* "ስሑት አስተያየቶች" ላይ ሒሳዊ ፍካሬ

*ገዛኸኝ ጸጋው**

**አጠቃሎ፡-** *ይህ ሒሳዊ ፍካሬ÷ ፍቅር እስከ መቃብርን አስመልክቶ በ**ብሌን** (1982) ወይይት ላይ የሥነ ጽሑፍ መምህራኑን (የዘሪሁን እና የደበበን 1982) ዕይታዎች መነሻ ያደረጉ ሦስት ጥቃቅን ሁነቶችን መዞ÷ ለመነሻዎቹ ጥያቄያዊ ሐቲቶች ምላሽ ለማርቀቅ ሞክሯል፡፡ ሒሳዊ ጥናቱ÷ ሦስቱን ገጸባህርያት ማንጸሪያ ያደረጉ ተናጠላዊ ሁነቶች ለመፈከር÷ በዮናስ (1992) ጥናት ላይ ተግባራዊ ከሆኑ የመፈከሪያ ሥልቶች ጋራ፣ የአንባቢ ምላሽ ሒስን (Reader-Response Criticism) አግባብቶ፣ በፊት ለፊት ከሚነገረን ጀርባ ያለን "ትርጉምና አንድምታ (meaning and significance) ፈልፍሎ ማውጣት" የሚያስችልን የፍካሬ (interpretation) ሥልት ተግባራዊ አድርጓል፡፡ በፍካሬ ሂደቱም÷* **አንደኛ፡-** *ሰብለ በዛብህን÷ "በፍቅር ጓደኝነት የተቆራኘችው የባላባት ዘር ሲነፍጓት፣ አማራጭ ስታጣ ነው" የሚለው የሐያስያኑ ምልከታ÷ የሰብለንም ሆነ የልቦለዱን ዐውዶች ያላገናዘበ÷ ርዕዮተ ዓለማዊ ወገንተኝነት የተጫነው "ስሑት አስተያየት" መሆኑን፤* **ሁለተኛ፡-** *የፊታውራሪ መሸሻን ከፈረስ ላይ ወድቀው መሞትን ከግላዊ ባህርያቸው የሚመነጭ ተምሳሌታዊ ሞት በማድረግ ሀዲስ የተሳካላቸው መሆኑን፤* **ሦስተኛ፡-** *የካሣ ዳምጤ "ጉድ" መባል አስመልክቶም÷ ደራሲው የገጸባህርይውን አፈንጋጭነት በውል የተገነዘቡ መሆናቸውንና በማፈንገጡ ጥያቄ እንዳያስነሳ "ጉድ" ብለው ለመሰየም መብቃታቸውን፤ ሒሳዊ ጥናቱ÷ በበቂ አስረጆች ለማጠየቅና ለመፈከር ሞክሯል፡፡ ፍቅር እስከ መቃብርም እንዲሁ ላይ ላዩን ብቻ ተነቦ የሚተነተን ሳይሆን÷ እያንዳንዱን ቅንጣት አህድ በተናጠልና በጥቅል እያነበቡና እየመረመሩ የሚፈከሩት "የሐሳቦች ልቦለድ" መሆኑን÷ ይህም ሒሳዊ ጥናት መጠቆም ይወዳል፡፡*

## *የጥናቱ ፈር መያዣ*

*ለመጀመሪያ ጊዜ በ*1958 *ዓ.ም. ለህትመት የበቃው የሀዲስ አለማየሁ* ***ፍቅር እስከ መቃብር****÷ በሀገሪቱ የሥነ ጽሑፍ ታሪክ የተለየ ምዕራፍ እንደከፈተ ተነግሮለታል፤ ይነገርለታል:: በብዙ የሥነ ጽሑፍ ባለሚሎች በተደጋጋሚ ይመሰገናል፡፡ ለሥነ ጽሑፍ ትምህርት ማስተማሪያነት ካገለገሉና ብዙ ጥናታዊ ሥራዎች ከተሠሩባቸው የሀገራችን ረጅም ልቦለዶች ውስጥ በግንባር ቀደምነት ይጠቀሳል:: በኢትዮጵያ የሥነ ጽሑፍ ምርምር ታሪክ÷ ሀዲስ ዓለማየሁ÷ የበርካታ ሐያስያንን እና ተመራማሪዎችን ትኩረት የሳቡ ስለመሆናቸው በተደጋጋሚ ይወሳል፡፡ እስከ* 1996 *ዓ.ም. ድረስ ብቻ የዶክትሬት ድግሪን ጨምሮ* 70 *ያህል የዲግሪ ማሟያ ምርምሮች ተደርገዋል፤ በተለይ በፍቅር እስከ መቃብር ላይ፡፡ በርግጥ አንዳንዶች÷ ከሌሎች ደራስያን መጻሕፍት ጋራም በንጽጽር አጥንተዋል* (*ኤልያስ* 1996)፡፡

*የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ሲታወስ ብዙ ጊዜ÷* ***ፍቅር እስከ መቃብር*** *መታወሱ አይቀርም፡፡ የእነ ደብረወርቅ፣ ዲማን፣ ማንኩሳ ወዘተ. ማኅበረ ባህላዊ ወመልክዓ ምድራዊ ገለጻ እያስቃኘ ያን "የገነገነና የሻገተ የፊውዳል ሥርዓት" ከማሳየቱ አንስቶ÷ በውስጡ እየተላወሱ ሰዋዊ ባህርይን ተላብሰው በተደራስያን አእምሮ የአይረሴነት አሻራቸውን እስከሚያሳርፉት ሕያው ገጸባህርያቱ ድረስ÷ መቼቱን ጠብቆ በሥርዓት ከሚቀዳው የቋንቋ ውበት አንስቶ÷ የሥርዓቱን የሳንሱር ክርን አልፎ ለህትመት እስከ መብቃቱ ድረስ÷ በብዙ የሥነ ጽሑፍ ሐያስያን ከግማሽ ምዕት ዓመት በላይ እያወያየ መዝለቁን ከዚህ በታች በቀረቡ ዋቢዎች ለማሳየት ተሞክሯል፡፡*

* ገዛኸኝ ጸጋው (ፒኤችዲ.) የሥነ ጽሑፍና ፎክሎር መምህር÷ በኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበር የ***ብሌን*** (የሥነ ጽሑፍና ፎክሎር መጽሔት) ማኔጂንግ ኤዲተር፡፡

“አስትሮሎጂ” በሚባለው የከዋክብት ሐተታ ገጸባህርያትን ከዘመን እና ከሀገር ጋራ እያናበቡ ጭምር መፈከር[1] እንደሚቻል÷ የተለያዩ ሐቲቶችን በማዋቀር በተግባር *በይነ-ዲሲፕሊናዊ የሥነ ጽሑፍ ንባብን* ለማበረታታ የታተረው የአብነት (2007) ***ፍካሬ ኢትዮጵያ*** መጽሐፍ÷ የግማሽ ምዕት ዓመት ባለጸጋውን÷ *ፍቅር እስከ መቃብርን* አስመልክቶ [ለንባብ በበቃ÷ በ49ኛ ዓመቱ ላይ] የሚከተለውን ብሏል፤

> **ፍቅር እስከ መቃብር** ቅኔ የሆነ ልቦለድ ነው፡፡ ሰምና ወርቅ ነው፡፡ ሰሙ በእንባና ሳቅ የተለወሰ ጣፋጭ የፍቅር ታሪክ ነው፡፡ ወርቁ ግን የኢትዮጵያ ታሪክ ትርጉም ነው፡፡ ረቂቅ ፍልስፍና እና ትንቢታዊ ድምጽም አለበት፡፡ ስለዚህ ትርጓሜ ያስፈልገዋል፡፡ ፍካሬ ሊኖረው ይገባል፡፡ ሰሙን አቅልጦ ወርቁን ሊያሳይን የሚችል አንድምታዊ ለምለም የትርጓሜ እሳት ማቀጣጠል ያስፈልጋል (ገጽ 288)፡፡

*ሥርግው* (2003፡ xvi) *ለመጽሐፈ ትዝታ* በጻፉት “*መግቢያ* 1” ላይ *ደግሞ*÷ “…*ጥንታዊት ኢትዮጵያን በመስታወት ማየት የሚፈልግ ፍቅር እስከ መቃብርን*÷ *ጥንታዊት ኢትዮጵያን ፊት ለፊት በአካል ማየት የሚፈልግ ደግሞ መጽሐፈ ትዝታ ዘአለቃ ለማን እንዲያነብ እመክራለሁ*” እንዲሉ÷ የዚህን ጽሑፍ አቅራቢ ወደ እዚህ ጥናት ከገባ በኋላ÷ “*አንዳንድ ግርምት*” የጫሩበት ምክንያቶችንም ታዝቧል፤ ለምሳሌ፡- *ፍቅር እስከ መቃብር* ለብዙ የሥነ ጽሑፍ ወዳጆችና አንባቢዎች በየጊዜው እንደ አዲስ ሆኖ መታየቱ፣ ስለ መጽሐፉ ቢወራ÷ ቢተረክ እንደማይሰለችና በተደጋጋሚ የሚነበብ መሆኑ (ዮናስ 1992)፣ በኢትዮጵያ ሬዲዮም ከሁለት ጊዜ በላይ መተረኩ፣ በተለይም ደግሞ ማንበብና መጻፍ የማይችለው “*መሃይሙ*” እንኳ÷ ስለ መጽሐፉ ኢምንት ያህል የሚያወጋው ያለማጣቱ፣ መጽሐፉ÷ **እንደ አዲስ ሆኖ የመታየቱን ሐቲት**[2] የሚያጸኑለት ይመስላሉ፡፡

በአማርኛ *ሥነ* ጽሑፍ ላይ ጥናት ያደረጉ የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ተመራማሪዎች÷ የአፈወርቅ ***ልብ ወለድ ታሪክ*** (*ጦቢያ*)÷ ቀዳሚው የፈጠራ (ልብ ወለድ) ድርሰት ስለመሆኑ እንጂ÷ በቀዳሚ ረጅም ልቦለድነቱ ላይ ጥያቄ እንዳላቸው ታይቷል፡፡ የብዙዎቹ ጠያቂዎች መነሻ ደግሞ÷ *ፍቅር እስከ መቃብር* እንደሆነ ጥናቶች አመላክተዋል (ገዛኸኝ 2002)፡፡ ለምሳሌ፡-ቶማስ ኬን÷ *ጦቢያን* ልቦለዳዊ ጽሑፍ (“fictional writing”) መሆኑ ጠቅሰው÷ እውነተኛ የመጀመሪያ የአማርኛ ረጅም ልቦለድ (“the first genuine novel in Amharic…”) ***ፍቅር እስከ መቃብር*** መሆኑን ያትታሉ (Kane 1975፡ 14)፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ÷ ፍቅሬ (Fikre 1983፡ 281) የአፈወርቅን *ጦቢያ*÷ **ሀገረሰባዊ ተረት** (folktale) እንደሆነ እና የመጀመሪያው የአማርኛ እውነታዊ ልቦለድ (realistic novel) ግን÷ *ፍቅር እስከ መቃብር* ስለ መሆኑ÷ በተለያዩ ጥናታዊ ሥራዎቻቸው መጠቆማቸውን ያስታውሷል[3]፡፡

ሌላው ስለ ***ፍቅር እስከ መቃብር*** የተለየ የሥነ ጽሑፍ ቅርስነት ከመሰከሩ ምርምሮች መካከል÷ ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበው የፈቃደ (Fekade 1988) የምርምር ድርሳን ተጠቃሽ ነው፡፡ በኢትዮጵያውያን ልቦለዶች ውስጥ (ከ1922-1966) ምሁራን ገጸባህርያት ምን እንደሚመስሉ በተፈተሸበት በዚህ ምርምር ውስጥ *ፍቅር እስከ መቃብር* ቀሳውስት፣ መነኮሳት፣ ደብተራዎችና አለቆች ገጸባህርያት በምሁርነት እንደቀረቡ አውስቷል፡፡ ከጉዱ

---

[1] መፈከር ወይም ፍካሬን አስመልክቶ፣ የደስታ ተክለ ወልድ÷ *ዐዲስ፡ ያማርኛ፡ መዝገበ፡ ቃላት*÷ “ፍካሬ፤ ትርጓሜ፡፡ ከዳዊት፡ አርእስት፡ አንደኛው፡ መዝመሪያው፡፡” (1962፡976) በማለት ይፈታዋል፡፡

[2] ቴዎድሮስ (2001፡186)፣ “‹ፍቅር እስከ መቃብር› ማለት መቃብር እስኪደርስ ያለ ፍቅር ማለት አይደለም፡፡ እስከ መቃብር የሚዘልቅ፣ በመቃብር ውስጥም የማያባራ ‹ተአምራዊ› ፍቅር ማለት ግን ነው፡፡ ይህ ፍቅር፣ ይህ ኅብረት፣ ይህ አንድነት ነባሩን ቅርበታቸውን እና ፍቅራቸውን የሚያውቀውን ጉዱ ካሳን ጭምር እስከማስደንገጥ የበረታ ነው” በማለት የሰብለን ነቢባዊና ገቢራዊ ሰብእና ጨምቀው÷ የመጽሐፉን ርእስ እና/ወይም ዋና ርእሰ ጉዳይ በሌላኛው መልኩ እንዲታይ፣ በይነ አህዳዊ ፈር ተልመዋል፡፡ በትልሙም÷ ሞትና ሕይወት ከተዛነቁበት ሰብለ ወጌላዊ የኑሮ ዕጣ ፈንታ ውስጥ÷ የመጽሐፉን ርእስ እንደ አዲስ የሚበይን ፍካሬ መፈንጠቃቸውን ያስተውሏል፡፡

[3] *Silence is not Golden* (1995) የሚለው የሥነ ጽሑፋዊ ምርምሮች መድበል፣ የአፈወርቅን የመጀመሪያ የአማርኛ ልቦለድ ደራሲነት የሚያጸኑ ጥናቶችን አካቷል፡፡ መጽሐፉ፣ የአካዳሚያዉን ዓለም አካዳሚያዊ ነጻነት ለማሳየትም ሆነ የተለያዩና የሚቃረኑ የሥነ ጽሑፍ ሒሶችና ንድፈ ሐሳባዊ ማንጸሪያዎች መኖራቸውን ለማጠየቅ ጥሩ ምሳሌ የሚሆን ይመስላል፡፡ ታዬ እና ዮናስ (1995) የፍቅሬን (1983) ጥናት እየሞገቱ፣ የአፈወርቅን *ጦብያ* የመጀመርያ ረጅም ልቦለድነት ባጸኑበት በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ÷ ፍቅሬ ደግሞ÷ “Realism in Haddis Alemayehu” በሚለው ጥናታቸው *ፍቅር እስከ መቃብር* የመጀመርያው እውነታዊ ረጅም ልቦለድ (“The first realistic novel”) እንደሆነ አስርድተዋል፡፡ የሦስቱ ሐያስያን ጥናቶች÷ የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ምርምሮቻቸው ላይ የተመሠረቱ መሆኑ ያመሳስላቸዋል፡፡

ካሣ በቀር አብዛኞቹ ምሁር ገጸባህርያት ዘማዊ፣ ጉቦኛ፣ አድርባይ እንደሆኑ፣ ቤተ ክርስቲያኗም ለፊውዳል ከበርቴዎች አቀንቃኝ እንደሆነች አሳይቷል፡፡

የፈቃደ (Fekade 1988) ምርምር:

> *Hadis Alemayehu has created a committed peasant leaders with a strong sense of justice instead of the intellectual leaders portrayed in Addis Alem, Agazi and Araya. That is why we said Hadis attempets togive an endogenous solution to an endogenous problem by involving the people directly concerned with it. This is one of the interesting insights in the novel* (Fekade 1988: 232).

በማለት ***ፍቅር እስከ መቃብር***÷ የፊውዳሉን ሥርዓት የሞገቱ÷ እነ አበጀን የመሰሉ ያመፁ ገበሬ ገጸባህርያትን ዋቢ እያደረገ÷ በሀገርኛው ወይም በሀገረሰቡ አማካይነት÷ ለሀገር በቀሉ ችግር÷ ሀገር በቀል መፍትሔ ለመጠቆም የሞከረ የመጀመሪያ ረጅም ልቦለድ ነው ብሎታል፡፡

በሌላ በኩል÷ ለዲግሪ ማሟያ ከተሠሩት ጥናቶች ውጭ ሁለት ሥራዎችም በጥንቃቄ ተመርምረዋል፡፡ አንደኛው÷ የደራስያን ማኅበር በ1982 ዓ.ም. ባሳተመው ***ብሌን*** መጽሔት ላይ "ያማርኛ ልቦለድ እድገት- ከ‹ጦቢያ› *እስከ* ‹ሓደፍርስ›" በሚል የቀረበ ውይይት (*ፍቅር እስከ መቃብር* ላይ የቀረበውን ብቻ ይመለከታል) ሲሆን÷ ሁለተኛው÷ የዮናስ አድማሱ (1992) "‹አስረኛንኩዋ?› ሀዲስ ዓለማየሁና የማኅበራዊ ሂስ ሥልታቸው" የሚል የምርምር ጽሑፍ ነው፡፡ እነዚህ ጥናቶች÷ ለዚህ የሒሳዊ ጽሑፍ አንኳር ሚና አላቸው፤ መነሻና መሠረትም ናቸው፡፡ "ለምን? እንዴት?" የሚሉ ጥያቄዎች መነሳታቸው አይቀርምና ምላሾቹን እነሆ፡፡

በመጀመሪያ በ***ብሌን*** ላይ የመጣውን የውይይት ነጥብ ስንመለከት÷ የመጽሔቱ አዘጋጆችም ሆኑ በውይይቱ ላይ የተሳተፉት ምሁራን ("ጓዶች") በሀገሪቱ የሥነ ጽሑፍ ታሪክ ላይ ጠንካራ አሻራቸውን ያሳረፉ÷ የፈጠራን ሥራ መሄስ ብቻ ሳይሆን የራሳቸውንም መከተብ የቻሉ÷ ጥበቡን በፅንሰ ሐሳባዊ መታገጊያ ቀንብበው የመረመሩና ንድፈ ሐሳቦችን የከለሱ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ጭምር በመሆናቸው (ዘሪሁን እና ደበበ 1982 ይመልከቱ)÷ የእነርሱን ሒሳዊ ውይይት መመልከት ተገቢ ነው፡፡ የእነዚህ ምሁራን ዕይታ÷ በተለይ ከውይይቱ በኋላ በተሠሩ ሥነ ጽሑፋዊ ሒሶችና ምርምራዊ ጽሑፎች ላይ የራሱን ውሱን ጥላ እንዳጠላ (bias እንደፈጠረ) የጠቆሙና ከምሁራኑ "የተለመደ" ዕይታ አፈንግጠው የራሳቸውን የፍካሬ ስልት ያመላከቱ ባለሙያዎች አልጠፉም (ቴዎድሮስ 2001 *ሀ* እና *ለ*፤ ዮናስ 1992፤ ብርሃኑ 1992)፡፡

የአብዛኞቹ ተማሪዎች ሥነ ጽሑፋዊ ሒሶች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ባለሙያዎቹ በውይይቱ ያነሷቸው ሐሳቦች ላይ እንደሚያጠነጥኑና በሐያስያኑ ውይይት ተጽዕኖ ሥር እንደወደቁ (ፈጠነ 1996፤ ኅብረት 1993፤ ይልማ 1986፤ Girma 2002 ይመለከቷል) የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ÷ ተመልክቷል፤ የራሱን ገጠመኝ አስታውሶም÷ የሐያስያኑና የመምህራኑን ሐሳብ "እንደመጨረሻ ፍጹም ትክክለኛ ሒሳዊ ትንታኔ" አድርጐ መመልከቱን ታዝቧል፡፡ ለዚህ ነው÷ ተማሪዎች (ሌሎች የሥነ ጽሑፍ ባለሙያዎችና ወዳጆች) በውይይቱ ላይ አስተያየት የሰጡባቸውን÷ *ፍቅር እስከ መቃብር* ዓይነትን መጻሕፍት ሲገመግሙ÷ ሲሔሱ÷ በተደጋጋሚ ሐሳባቸውም ሆነ አስተሳሰባቸው÷ **በአንድ አቅጣጫ ብቻ የተቀየደ ይመስላል መባሉን የሚጋራዉ**[4]፡፡ ሌላ የምርምር ፈለግና ዱካ ከመከተል ይልቅ

[4] "… ከሥነ ጽሑፍ ኪንና ትምህርት ፍጥነት አንጻር፣ እንደ ***የስነጽሁፍ መሰረታውያን*** [1992] ካለ ጥቂት ለማይባል ዘመን ትውልድን ካገለገለ (ቅድመ ኅትመት ከ1985-1991 በማስተማሪያ ጽሑፍነት አገልግሏል)፣ ዓላማውም በመግቢያው እንደተጠቆመው ‹ከስነጽሁፍ ጋር ለመተዋወቅ ለሚሹ አንባብያን በቂ ግንዛቤ ለማስጨበጥ› ከሆነ መጽሐፍ የምንጠብቀውን ያህል ጽንሰ ሐሳባዊና ንድፈ ሐሳባዊ ጥንካሬ ማግኘት የቻልን አይመስለኝም" በማለት ቴዎድሮስ (2007፡33)፣ የዘሪሁንን (1992) መጽሐፍ በአጽንኦት የሔሰው መሆኑን ያመሳክሯል፡፡ በርግጥም መጽሐፉ÷ የሥነ ጽሑፍን ሁለንተናዊና በይነ ዲሲፕሊናዊ ተፈጥሮ ያለመረዳትና ቀመራዊ አድርጎ የማሰብ አካሄዶችን ሲከተል ይስተዋላል፡፡ ይህ የቀመራዊነት ጣጣው ደግሞ፣ "ብልሹ ለሚላቸው ቅርጾች ጭምር ምሳሌ እስከ መፍጠር የሚያደርስ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ አቀራረብ ቢያንስ ቢያንስ የሚከተሉት ትችቶች ያገኙታል፡፡ አንደኛ፣ እጅግ አከራካሪ ለሆነ ጉዳይ ህልው የሆነውን

ለምሳሌ፡- *የፍቅር እስከ መቃብር*÷ ጭብጥ፤ የገነነውን የፊውዳል ሥርዓት "በሚገባ እንደሚያንፀባርቅ" ተደርጐ ብቻ÷ **አንዳዊ አመለካከት**[5] በተደጋጋሚ ሲስተጋባ የሚሰማዉ፡፡

በሁለተኛነት የምናነሳው÷ "‹አስረኛንኩዋ?› ሀዲስ አለማየሁና የማኀበራዊ ሂስ ሥልታቸው" የተሰኘውን የዮናስን (1992) ሥራ ነው፡፡ ጥናቱ÷ እስከ አሁን ሲተኮርበት ከነበረው የሥነ ጽሑፍ ሒስ አካሄድ የተለየ÷ አዲስ የምርምር አቅጣጫን የተለመ÷ የእነ ደበበን (1982) አንዳዊ ዕይታየሞገተ ሒስ ነው፡፡ "እንዴት?" ለሚለው ከተወሰኑ ነቁጦች አኳያ÷ በ*ብሌን* (1982) ከቀረበው ውይይት ጋር በንጽጽር እንየው፡፡ በውይይቱ ላይ የነበዛብህ የፍቅር ታሪክ ለመጽሐፉ ዋና ማጠንጠኛ ለሆነው የፊውዳል ሥርዓት ማሄጃ (vehicle) ሆኖ ቀርቧል፡፡ በዮናስ (1992) ጥናት ላይ ደግሞ÷ የፊውዳሉም ሆነ የፍቅር ታሪኩ÷ ለጥቃቅኖቹና ረቂቆቹ ፍልስፍናዊ ሐቲቶች ወይም ሐሳቦች ማሄጃ እንደሆነ ተጠቁሟል፡፡ አትኩሮቱም÷ ጥቃቅን በሚመስሉ ዳሩ ግን ጥቅሉን የመጽሐፉን ጭብጥ ለመፈከር በሚያስችሉ የተበታተኑ "የንባብ አሀዶች" (Reading units) ላይ ነው፡፡

በ*ብሌን* ላይ÷ *ፍቅር እስከ መቃብር* የፊውዳሉን ሥርዓት አስከፊነት የሚገልፅ÷ ውድቀቱንም እንደ ደረቅ ትንቢት የሚጠቁም ብቻ ተደርጎ ቀርቧል፡፡ በዮናስ (1992) ሥራ ላይ ደግሞ÷ የመጽሐፉ ጭብጥ ይህ ብቻ ነው ብሎ መወሰን ተገቢ እንዳልሆነ በመጠቆም÷ የተለያዩ የንባብ አሀዶችን መሠረት አድርጐ የሰዎች "የሰብእና መንጠፍ" (dehumanization) አይሎ እንደሚገኝ አመላክቷል፡፡ ስለሆነም የዮናስ[6] ሒሳዊ መጣጥፍ÷ በጥናት አካሄዱም ብቻ ሳይሆን÷ በጭብጥ ግኝቱም አዲስነት አለው ማለት ይቻላል- በባጭሩ፡፡

በዚህ ሒሳዊ ጥናት÷ በ*ብሌን* ላይ በእነ ዘሪሁን እና ደበበ (1982) የቀረበዉ ውይይትም ሆነ የዮናስ (1992) ሒሳዊ ምርምር በአስተውሎት ተፈትሸዋል፡፡ አንደኛው (የእነ ዘሪሁን 1982)÷ ለዚህ ሥነ ጽሑፋዊ ሒስ ማንጸሪያ የሚበጁ ሞጋች የመነሻ ጥያቄዎች ረቀውበታል፡፡ ሌላኛው ለዚህ ሒሳዊ ጽሑፉ ማተገጊያ÷ ለአካሄዱ መግሪያ የሚሆን የፍካሬ ስልቶችና አተገባበሮች ተሰንቀውበታል፡፡ እናም÷ የዚህ ጥናት አቅራቢ÷ በ*ብሌን* (1992) በ*ፍቅር እስከ መቃብር* ላይ ከቀረበው ውይይት÷ በአብዛኞቹ ሐያስያን ስሙዓን (acceptable) የሆኑ አስተያየቶችን መላልሶ በመመርመር÷ ሦስት የመነሻ ጥያቄዎችን አንስቷል፡፡ የዚህ ሒሳዊ ጥናት ዓላማም÷ በሥነ ጽሑፍ መምህራኑ ሒሶች ላይ ሌላ ሒሳዊ ሙግት በማጫር እና የተለያዩ ጥቃቅን የሚመስሉ ሁነቶችንና ሁኔታዎችን ወይም አሀዶችን በመፈከር ለመነሻ ጥያቄዎቹ ምላሽ ማርቀቅ መሆኑ ይታወሳል፡፡

**ፍካሬ**

በዚህ ክፍል የሚነሡ **ሦስት** ነጠላ ጉዳዮች ከ*ፍቅር እስከ መቃብር* ጥልቅ የሐሳብ ባሕር ውስጥ በስሱ ተጨልፈው የወጡ ሦስቱ የመነሻ ጥቃቅን ሁነቶች ወይም የገጸባህርያት አሳሳልን ማንጸሪያ ያደረጉ ጥያቄያዊ ሐቲቶች ናቸው፡፡ ይህ ሥነ ጽሑፋዊ ሒስ÷ የመምህራኑን ዕይታዎች መነሻ ያደረጉትን እነዚህን ሦስት ተናጠላዊ ሁነቶች ለመፈከር÷ ቀደም ሲል እንደተጠቆመው የዮናስ (1992) ጥናትን እንደ ማንጸሪያና ፈር መያዣ አድርጎ ተጠቅሟል፡፡

---

ሥነ ጽሑፋዊ መረጃ ቸል ብሎ የራስን መረጃ መፈብረክ አንድም የእምነት ጥያቄ ያስነሳል፡፡ ሁለተኛ፣ ሚዛኑ ራሱ ያረጀ ያፈጀ ነው" (ቴዎድሮስ 2007፡ 34) መባሉን ማጤን ያስፈልጋል፡፡

[5] "ቁዘማ፣ ባህል እና ልማት በኢትዮጵያ" የሚለው የፈቃደ (2004፡ 7) ምርምራዊ ቁዘማ ውስጥ፣ ሰዎች የተለያዩ አማራጮች በማየት ፋንታ፣ "አንድ ነገር ወይ ነጭ ነው ወይ ጥቁር ብቻ ነው፡፡ … ወይ ጥሩ ወይ መጥፎ …" የሚለውን አመለካከት ማራመዳቸው የተሔሰበት፣ የቆዛሚው ምስርት ማንጸሪያ ነው (*Economic Focus*. VOL.7, NO. 2 June 2004. LISAN Printing Press)፡፡

[6] እነ ቶማስ ኬንን (Kane 1975) የመሰሉ የውጭ ሀገር አጥኚዎች፣ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ሥራዎችን "መርምረው" የሥነ ምግባር ሰባኪነት (Didactism) ይገንባቸዋል፣ እውነታዊም (Realistic) አይደሉም ወዘተ. በማለታቸው÷ ዮናስ÷ "On the State of Amharic Literary Scholarship" (Yonas 2001) በተባለ ጥናታቸው÷ የተመራማሪዎቹን ድፍረት ለመሞገትና የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ የራሱ የአነባበብ ሥልት እንዳለው ለማመላከት የቻሉ÷ የሥነ ጽሑፍ መምህርና ተመራማሪ መሆናቸው ይታወቃል፡፡

አብራምስ (Abrams 1999) ስለ አንባቢ ምላሽ ንድፈ ሐሳብ ያነሱት ነጥብም÷ በዮናስ (1992) ጥናት ላይ ተግባራዊ ከሆኑ የመፈከሪያ ሥልቶች ጋራ አብሮ ሊሄድ ስለሚችል÷ የፍካሬ ሥልትን የንድፈ ሐሳብ መሠረት ለመረዳት መልካም አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ በተለይም አንድ ነጠላ ሁነት (episode) ወይም "ቴክስት" (text) በራሱ ለመነበብ በቂ እንደሆነና አንብቦ ለመፈከር የእያንዳንዱ አንባቢ ግላዊ ምልከታ ወሳኝ እንደሆነ መጠቆሙ÷ የዚህ ሒሳዊ ጽሑፍ አቅራቢ÷ ወደዚህ "የሒስ ላይ ሒስ" ወደሆነዉ የሥነ ጽሑፍ ፍካሬ በድፍረት እንዲገባ ብርታት ሆኖታል፡፡

ዮናስ (1992፡ 78)÷ "ልብ ወለድን ማንበብ ማለት÷ በፊት ለፊት ከተነገረን ጀርባ ያለውን ትርጉምና አንድምታ (meaning and significance) ፈልፍሎ ማውጣት ማለት ነው፡፡ ይህንን ተግባር ፍካሬ (interpretation)" እንደሚሉት ጠቁመዋል፡፡ በጥናታቸው መግቢያ ላይም÷ ሾፐናወር (Schopenhauer) የሚባለውን የጀርመን ፈላስፋ አባባል÷ "The business of the novelist is not to chronicle great events but to make small ones interesting" በማለት ጠቅሰው÷ የአንድ ደራሲ ተግባር ታላላቅ የሆኑ ወይም የሚባሉ ሁነቶችን ከመመዝገብ ይልቅ÷ ጥቃቅን የሆኑትን አዋዶና አመጣጥኖ ማቅረብ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

ጥቅሱም÷ ጥቃቅን የሚመስሉ ግን ተዋህደው ታምር የሚፈጥሩ ጉዳዮችን እንድናስተውል የሚያነቃ ሐሳብ ነው ማለት ይቻላል[7]፡፡ በመሆኑ ይህ ሒሳዊ ፍካሬ፤ *ፍቅር እስከ መቃብርን* አስመልክቶ በብሌን (1982) ከቀረበው አጠቃላይ ወይይት ላይ ሦስት ጥቃቅን ሁነቶቸን ("ስሑት" የሚመስሉ አስተያየቶችን) መዞ በማውጣት÷ ገጸባህርያቱን ማንጸሪያ አድርጎ÷ የተጣነኑ ያላቸውን የሐያስያኑን ምልከታ በሚያቃና እና በሚያቀና መልኩ እንደሚከተሉት ትርጓሜዎችን ይፈክራል- ያረቃል፡፡

### ***ሀ. ሰብለ ወንጌል÷ እንደ ማንጸሪያ***

*የባላባት ዘር ሲነፍጋት÷ አማራጭ ስታጣ ነው በዛብህን በፍቅር ጓደኝነት የተቆራኘችው?*

ይህ ሰብለ ወንጌል ተኮር የመነሻ ጥያቄ የተገኘው÷ ቀደም ሲል በመግቢያው ላይ እንደተጠቆመው የሥነ ጽሑፍ ባለሙያዎቹ ባደረጉት ውይይት ላይ ደበበ (1982፡) ከተናገሩት አስተያየት ነው፡፡ ደበበ (ገጽ÷29)÷ "… ፍቅር ከመደብ ውጭ አይደለም፡፡ ተስፋ በመቁረጧ፡ ወንድ በመነፈጓ በዛብህ ብቸኛ ምርጫዋ ስለሆነ እንጂ ከሌላ የፊታውራሪ ልጅ ጋር ብትገጥም እሱን ነበር የምትመርጠው፡፡ ምርጫ የሚል ጥያቄ ቢነሳ የወላጆቿ ምርጫ የእርሷም ምርጫ ሊሆን ይችል ነበር…" በማለት የሰብለን ሰብእና የሚፈታተን ሐሳብ አቅርበዋል፡፡ ይህንን ጉዳይ ከተወያይ የሥነ ጽሑፍ መምህራን አንዱ የሆኑት ዘሪሁን አስፋውም (ገጽ÷29)÷ "ልቦለዱ ውስጥ አንድ ቦታ የመንደር ሴቶች ናቸው መሰለኝ ስለ ሰብለ ወንጌል ሲናገሩ፡- **‹ምን ታድርግ እንጀራ ቢከለከሏት በቅርብ ያገኘችውን ቆሎ ሰረቀች›** ብለዋል፡፡ ይህ ጓድ ደበበ … ለሚለው ነጥብ ድጋፍ ነው…" (አጽንኦቱ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ነው) በማለት አጠናክረውታል፡፡

የዚህ ሒስ አቅራቢ ግን÷ የደበበ እና የዘሪሁን አስተያየቶችን ተቃርኖ÷ በሌላ መንገድ ለመሞገትና አስተያየቶቹን ገልብጦ ለመፈከር ይሞክራል፡፡ ሰብለ በባላባታዊ ሥርዓትም ሆነ÷ በባላባት ዘር ላይ ያላትን ዐቋም ብሎም ፍቅረኛዋ (የትዳር አጋሯ) ከየትኛው መደብ ቢወጣ እንደምትመርጥ÷ በመጽሐፉ በተለያዩ ቦታዎች የቀረቡ ሐቲቶችን መርጦ እንደሚከተለው ይፈክራል፡፡

---

[7] አንድ ረጅም ልቦለድ በደምሳሳው ሙሉ ታሪኩን እንዲህ ነው እያሉ እየደበላለቁ ከመናገር፣ ከመተንተን፣ ጥቃቅን ቅንጣት ሁነቶችን በተናጠል እየመረመሩ÷ ተዋህደው የፈጠሩትን ትልቅ ምስል ለመረዳት መሞከር÷ እንደ *ፍቅር እስከ መቃብር* ላሉት ፈርጀ ብዙ ልቦለዶች የበለጠ ተመራጭ የፍካሬ ሥልት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ከአንድ ረጅም ልቦለድ ውስጥ ጥቃቅን "የንባብ አሀዶችን" (Reading units) እየመዘዙ መተንተን÷ በክፍል ውስጥ ትንተናንና ፍካሬን ለማስተማር ብቻ ሳይሆን÷ በጠባብ አምዶች ላይ ለሚደረጉ ሒሳዊ ትንታኔዎችና ፍካሬዎችም የሚበጅና የሚስማማ ሥልት ነው ማለት ይቻላል፡፡ በርግጥ የፍካሬ ሥልቱ÷ በንባብ ውስጥ ብዙ መቆየትን፣ የተለያዩ የምርምር ሥራዎችን ማንበብን፣ የአካዳሚያዊ ዕውቀት ከሕይወት ልምድ እውነት እያዋደዱ የሚጽፉ ጸሐፍትንና ሐያስያንን ማማከርን ወዘተ. ሊጠይቅ ይችላል፡፡ አንዲት ነጠላ ሕዋስ በሕይወት ዑደት ውስጥ ያላትን ዋጋ ማወቅ÷ የፈጣሪነትን ሚና በግማሽ እንደመወጣት ይቆጠራልና፡፡ ፈጣሪነትን÷ ከድርሰትም ከሕይወትም ጋራ እያገናኙ መመልከት ይቻላል- ይገባልም፡፡

ገና ከመነሻው ሰብለ ወንጌል ያን ግብታዊ ሥርዓት እንድትሞግት በእርሷም ሆነ በሌሎች ላይ የሚደርሰውን የሰብእና መንጠፍ እንድትመሰክር ሆን ተብሎ በብልሃት የተቀረጸች ገጸባህርይ ናት፡፡ እንደ ወላጆቿ በአጥንትና በደም ያልተዋጀች÷ በሰው ልጆች እኩልነት የምታምን÷ ትምክህተኝነትን በፊት ለፊት የምትጋፈጥ "ታግሶ አጋልጤ" ናት፡፡ ይህን የግል አስተሳሰቧን አስመልክቶ ደግሞ በመጽሐፉ ከተወሳችባት ከመጀመሪያው የትውውቅ ምዕራፍ ጀምሮ÷ "ሰብለ ወንጌል… በትሕትና፡ በሰፊው፡ የታደለች፡ ስለነበረችና፡ **በባህርይ፡ ትምክህት፡ የምትጠላ፡ ከወላጆቿ፡ ፈጽማ፡ የተለየች፡** ነበረች… ከወይዘሮ፡ ጥሩ አይነትም፡ **ኩራታቸውንና፡ ግብዝነታቸውን፡** ብቻ፡ ለሳቸው፡ ትታ፡ የቤት፡ ባልትናቸውንና…" (ገጽ 84፤ አጽንኦቱ የሒስ አቅራቢው ነው) በማለት ደራሲው በሚገባ ገልጸዋታል፡፡

ሰብለ ኋላ ቀሩን ሥርዓት ትቃወምና ትኄስ ዘንድ ከተፈጥሯዊ አስተዋይነቷ ባሻገር÷ ከጉዱ ካሳ ጋር ያላት የጠበቀና የሰመረ ግንኙነት ትልቅ አስተዋጽኦ አለው፤ በባህርይውም በግብሩም ያስተምራታል (ታገልግልህ ተብሎ የተሰጠው÷ "አፈር ጠላቱ" የተባለችውን "ባሪያ" ÷ "እንቆጳዚዮን" ብሎ እንዳገባት ልብ ይሏል)፡፡ ይህን ጉዳይም ወላጆቿ በግልፅ ይናገራሉ፤ ለምታነሳው ጥያቄና ትችት ጉዱ ካሳን ነው ተጠያቂ ያደረጉት፡፡

ሰብለ ሰው በሰውነቱ እኩል ነው ብላ እንደምትቀበል፣ ባላገርም ሰው በመሆኑ ሊከበር እንደሚገባ÷ እራሳቸውን ለየት አድርገው የሚኮፍሱት አባቷም÷ ባላገር ከሚባለው ጋራ በሰብአዊነታቸው እኩል እንደሆኑ ወዘተ. (አባቷ በባላገሮች ተይዘው ወደ ማርቆስ በመሄዳቸው ዙሪያ ከእናቷ ጋር ስትጨዋወት) አቋሟን እንደሚከተለው በግልፅ አሳውቃለች፤ "… ልንገርሽ፡ እማማ፡ ብቻ፡ አይሙቱ፡ … ባላገር፡ ቢማርካቸው፡ በጣም፡ በጣም፡ ነው፡ ደስ፡ የሚለኝ፡፡ ምክንያቱን፡ ልንገርሽ? ባላገር፡ እንደሳቸው፡ ሰው፡ መሆኑን፡ አውቀው፡ ከባላገር፡ ጋር፡ ተስማምተው፡ በሰላም፡ የሚኖሩት፡ ኃይሉን፡ ሲያሳያቸው፡ ነው፡፡ **ያን ጊዜ ነው፡ ሰው፡ የሚሆኑት!"** (ገጽ 305÷ አጽንኦት የሒስ አቅራቢው ነው)፡፡

ከዚህ የመረረ ንግግሯ በተለይ አጽንኦቱ **("ያን ጊዜ ነው፡ ሰው የሚሆኑት!")** በጀርባው ስናነበው÷ እያገላበጥን ስንፈክረው የአባቷን ሰብአዊ ፍጡርነት እስከ መግፈፍ መድረሷን እንረዳለን፡፡ አሁን ላይ አባቷ÷ **"ሰው"** እንዳልሆኑ እየነገረችን ነው፤ ባይሆን÷ እንደ ብላታ ንጉሤ **"የቁዋያ፡ እሳት"** ወይም እንደ አበጀ በለው **"አውሬ"** አድርጋ እንደምታስባቸው እንጠረጥራለን፡፡ ይህም የባላባታዊውን ሥርዓት ወግና ልማድ እንዳንገሸገሻት÷ በዚህ ሳቢያም በአባቷ ላይ ሳይቀር የጭካኔ ሰይፍ አንዳስመዘዛት ያሳያል፡፡ ይህ ጥላቻ ደግሞ÷ "የባላባት ዘር÷ አጥንቱ የጠራ …" የሚባል ወንድ እስከ ወግ ልማዱ ጭምር እንደማትቀበለው ማስረገጥ ይቻላል፡፡ ለዚህ ደግሞ÷ ከበዛብህ ጋር ስላላት ግንኙነት አባቷ በጠየቋት ጊዜ ፍጹም በሆነ የመንፈስ ጥንካሬና ስሜት÷ "… ገበሬ፡ ሰው፡ ነው! የገበሬ፡ ልጅም፡ የሰው፡ ልጅ፡ ነው፡፡ የመኳንንት፡ ዘር፡ ጥሩ፡ የገበሬ፡ ዘር፡ ጉድፍ፡ መሆኑን፡ አውቆ፡ መኳንንት፡ የሚመርጥ፡ ይቸገርበት! እኔ፡ የገበሬ፡ ልጅ፡ የሚሉትን፡ እወደዋለሁ!…" (ገጽ 410) በማለት **ከእግዚአብሔር በላይ የሚፈሩትን** [እዚህ ላይ÷ የፊታውራሪን የንስሐ አባት÷ የአባ ሞገሴን ፍርሃትና መሽቆጥቆጥ ያስታውሷል] አባቷን ከሰው ፊት በድፍረት ትሞግታቸዋለች - ለመሥዋዕትነት ተዘጋጅታ፡፡

በሌላ በኩል÷ ዘሪሁን (ገጽ÷29) የሰብለን የባላባት ዘር ምርጫ ለማጠናከር÷ "… ምን ታድርግ እንጀራ ቢከለክሏት በቅርብ ያገኘችውን ቆሎ ሰረቀች ተብሏል" ያሉትም ቢሆን÷ ለሰብለ ወንጌል የቀረበ ሐሜት አይደለም (ፍ.እ.መ. ገጽ 90 ይመልከቱ)፡፡ ምሳሌውን በማቀራረብ ለሰብለ ይሆናል እንዳይባል እንኳ÷ በዛብህ የሚባል ሰው እስከ መፈጠሩ ባላወቀችበት ጊዜ የተነገረ በመሆኑ÷ ትንታኔያቸው አይሰምርም፡፡ ለነገሩ'ኮ ሰብለ÷ በዛብህንም ቢሆን ወዲያው አልመረጠችውም፤ እንደውም ይቀፋት÷ ያስጠላት ነበር፡፡ በኋላ ላይ ሲቀራረቡና አጠቃላይ ሰብእናውን የመመዘን ዕድሉ ሲያጋጥማት ግን÷ ምርጫዋ እንደሆነና ከነፍሷ እንደተቀበለችው ታይቷል፡፡

ሰብለ÷ በዛብህን ከልቡናዋ ጋራ መክራ÷ መርምራ ወደ ውስጧ ካስገባቸው በኋላማ÷ "የፍቅር ጽናቷ እና የልብ ስብራቷ የግርንግሪት ስላሰሯት ከበዛብህ መቃብር ርቃ መሄድ አትችልም፡፡ … ሰብለ ቃሏን ጠብቃለች፡፡ ‹በሄደበት እስክከተለው› ትበል እንጂ እመቃብር ቤት ገብታ የቁም ሞቷን እየሞተች በሄደበት ከተከተለችው ቆይታለች፡፡ ስለዚህ አለመለየቷ ፍጹም ነው" እንዲል የቴዎድሮስ (2001፡ 181-182) ፍካሬ፤ ፍቅሯ እስከ በዛብህ መቃብር

ብቻ አይደለም የዘለቀው፤ ከመቃብሩ በኋላ ሁሉ÷ እስከ ዘላለሟ ሁሉ አብሯት የሚኖር ሕያው ፍቅር ነው÷ በልቡናዋ እንዲጸድቅ የፈቀደችው፡፡

በአጠቃላይ የሰብለ ነገረ ሥራ የሚያሳየው÷ ምርጫዋን በዘልማድ ወይም በቤተሰብ ውትወታ ከምታካሂድ ይልቅ÷ በአስተውሎት በራሷ ዕይታ እንደምትወስን እና እንደወሰነችም ነው፡፡ በመሆኑም÷ ሰብለ በዛብህን የወደደችው÷ "በፍቅር ጓደኝነት የተቆራኘችው የባላባት ዘር ሲነፍጋት፣ አማራጭ ስታጣ ነው" የሚለው የመምህራኑ ምልከታ፤ የሰብለንም ሆነ የልቦለዱን ዐውዶች ያላገናዘበ÷ "ስለ መደብ ልዩነት" የሚያቀነቅን÷ ርዕዮተ ዓለማዊ ወገንተኝነት የተጫነው "ስሑት አስተያየት" ነው ማለት ይቻላል፡፡

## *ለ. ፊታውራሪ መሸሻ÷ እንደ ማንጸሪያ*

*"በባላገሮች ተደብድበው ቢገደሉ" የልቦለዱ ታሪክ ያረካ ነበር?*

ይህ ፊታውራሪ መሸሻን የሚመለከት የመነሻ ጥያቄ የተወሰደው÷ ቀደም ሲል በመግቢያው ላይ እንደተጠቆመው የሥነ ጽሑፍ ባለሙያዎቹ ባደረጉት ውይይት ላይ ዘሪሁን (1982) ከተናገሩት አስተያየት ነው፡፡ በውይይቱ ላይ መምህራኑ ምንም ዓይነት ማስተካከያና ተቃውሞ አንስተው ሳይከራከሩ÷ ዘሪሁን (1982፡ 32) የሚከተለውን ሐሳብ ሰንዝረዋል፡-

> … ጓድ መስፍን እንደተናገረው፡ ፊታውራሪ መሸሻን በሁኔታቸውና በእንቅስቃሴያቸው ልንወዳቸው እንችላለን፡፡ የምንወዳቸው ግን እንደተሳሉ በአቀራረፃቸው እንጅ በድርጊታቸውና በባህርያቸው አይደለም፡፡ አንባቢ ይቃወማቸዋል፡፡ **ሌላው ቀርቶ አሟሟታቸው የሚያናድደን ሰዎች አለን**፡፡ ምክንያቱም እንደ ባሕሪያቸውና ድርጊታቸው ቢሆኖ ኖሮ ከበቅሎ ላይ **[ፈረስ ተብሎ ይነበብ]** ወድቀው ከሚያልፉ **በባላገሮች ተደብድበው ቢገደሉ ነበር የሚያረካን፡፡** በዚህ መልክ ያልቀረበው የደራሲው ምርጫ ስለሆነ ነው (አጽንኦቱ÷ የዚህ ሒስ አቅራቢ ነው)፡፡

ከዚህ በላይ የቀረበው አስተያየት ገና ከመነሻው እርስ በርስ የሚጣረሱ ሐሳቦች ተንጸባርቀውበታል፡፡ ለምሳሌ፡- "… የምንወዳቸው ግን እንደተሳሉ በአቀራረፃቸው እንጅ በድርጊታቸውና በባህርያቸው አይደለም …" የሚለው ምን ለማለት እንደተፈለገ ግልፅ አይደለም፡፡ የአንድ ገጸ ባህርይ አቀራረጽ ሲወሳ ግብሩ ባህርይውን÷ ባህርይው ግብሩን እንደሚወስነው ይታወቃል፡፡ በሌላ አነጋገር÷ የገጸ ባህርይው አቀራረፅ በዋነኝነት የድርጊቱና የባህርይው ጭምቅ ነው፡፡ **የፊታውራሪ መሸሻን**[8] "አቀራረጽ ወደነዋል" ሲባል፤ ይሄው ግብሩንና ባህርይውን ወደነዋል ማለት ነው፡፡ የአንዱን ገጸባህርይ ህያውነት የሚያጠይቁ÷ ሥጋና ደም አልብሰው እስትንፋስ የሚዘሩ ጉዳዮች አይደሉምን? ግብርና ባህርይ፡፡

ገጸባህርይ እኮ የደራሲው ሐሳብ (Idea) ነው፡፡ ሐሳብ ደግሞ የማይታይ የማይጨበጥ ነገር ነው፡፡ ተጨባጭ ይሆን ዘንድ ግብርና ባህርይ አላብሶ በሕይወት ዑደት ውስጥ ማስጓዝ ግድ ይላል፡፡ የደራሲው ሐሳብ ነው የምንለው ገጸባህርይ÷ ባህርይውን ገልጠን÷ በድርጊት አኳሽተን ካላቀረብነው ምኑን ገጸባህርይ ቀረጽን!? ስለዚህ

---

[8] ይህን ስያሜ አስመልክቶ÷ **"የገፀባህሪያት ስሞች ስነፅሁፋዊ ፋይዳ በአማርኛ ልቦለዶች"** የሚለው የብርሃኑ (1991፡14) ጥናት÷ "ፊታውራሪ መሸሻ ግን የስማቸውን ዓይነት ሰው አይደሉም፡፡ የተራበን የተቸገረን የሚያስጠጉ ሳይሆኑ÷ ጨካኝ÷ በቃኝን የማያውቁ፤ የተጠቃን የሚደግፉ… ጉልበተኛ ናቸው" በማለት ስማቸውን ፈክሮታል፡፡ ጥናቱ÷ በአማርኛ ልቦለዶች ውስጥ የገጸባህርያት ስሞች ያላቸውን ሥነ ጽሑፋዊ ፋይዳ በትኩረት የመረመረ ሲሆን÷ "ትወራዊ ዳራ" ባየበት ክፍል÷ የገጸባህርያቱ የተጸውዖ ስሞች የገጸባህርይዉ ህልውና መሠረቶች እንደሆኑ የባርቴዝን÷ "The proper name enables person to exist out side themes, whose sum nonetheless constitutes it entirely" (Barthes 1947:134) በማጣቀስ የንድፈ ሐሳብ መሠረት ለመጣል ሞክሯል፡፡ ሁሉም የገጸባህርያት የተጸውዖ ስሞች የገጸባህርያቱ ህልውና መሠረት የማይሆኑባቸው አጋጣሚ ሊኖር እንደሚችል ቢታሰብም÷ የብርሃኑ ጥናት የየዘመኑን የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ይወክላሉ በተባሉ 20 ድርሰቶች ውስጥ ያሉ ወካይ የሚሆኑ የተጸውዖ ስሞችን በማስተንተን ለገጸባህርያት አጣጣል፣ ለትልም አወቃቀር፣ ለጭብጥ ግንባታ ያላቸውን ሥነ ጽሑፋዊ ፋይዳ የሚፈክር ምርምር መሆኑን መጠቆም ተገቢ ነው፡፡

ፊታውራሪ መሸሻን "እንወዳቸዋለን" ከተባለ መወደዱ የመጣው ከባህርያቸው መሆኑን መጠቆም ያስፈልጋል፡፡ በመጽሐፉ ላይ የሰፈረውን ሐሳብ ስንፈክረው ለተነሳው ሐሳብ ዋቢ ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል ባለሙያዎቹ÷ ፊታውራሪ መሸሻ የፊውዳሉ ባላባታዊ ሥርዓት ወካይ እንደሆኑ÷ የመጽሐፉም ዋነኛ ጭብጥ የፊውዳሉን ሥርዓት አስከፊነት ማጋለጥና የማኅበረሰቡንም ሆነ የሥርዓቱን የወደፊት ዕጣ ፈንታ "እንደ ደረቅ ትንቢት" መጠቆም እንደሆነ በውይይታቸው አስረግጠው ሲናገሩ ይሰማል፡፡ ታዲያ÷ የመጽሐፉ ጭብጥ ነው ያሉትን አስተያየት "ተቀብለን" እንኳ÷ የፊታውራሪን አሟሟት ስንመረምር÷ "በባላገር ተደብድበው ቢገደሉ ነበር የሚያረካ" ይህ የልሆነው ግን÷ "የደራሲው ምርጫ ስለሆነ ነው" በሚል ብቻ በአግድም የሚያልፉት ጉዳይ ሆኖ አይገኝም፡፡ ይልቁንም÷ መጽሐፉን ወደ ፊትና ወደ ኋላ መላልሶ በመፈተሽ አንዳች ማጠቃለያ ላይ መድረስ ይቻላል፡፡

እዚህ ላይ ካቫላሮ÷ አንድን መጽሐፍ እንዴት ማንበብ እንዳለብን÷ ፍንጮችን ከራሱ ከመጽሐፉ ማግኘት እንደምንችል÷ "That is, a text may give the reader clues and tips suggesting how it could or should be read." (Cavallaro 2001፡ 51) በማለት የመከሩትን ልብ ማለት ይገባል፡፡ የፊውዳሉን ሥርዓት መገርሰስ ለሚፈልጉና መጽሐፉም እንደ ደረቅ ትንቢት ጠቋሚ መሆኑን ለሚያምኑ "ተራማጅ ሐያስያን"÷ የፊታውራሪ ከአለት ላይ ተፈጥፍጦ ከመሞት የበለጠ÷ ከመጽሐፉ ሌላ መረጃ ፈልፍሎ ማውጣት እንዴት ይቻላቸዋል!? የፊታውራሪ አሟሟት'ኮ የፊውዳሉን ሥርዓት የሚገረስስ አብዮታዊ ትውልድ ይፈጠርም አይፈጠርም÷ ሥርዓቱ በራሱ እንደሚፈረካከስ የሚጠቁም "የደረቅ ትንቢት" መገለጫ ተምሳሌት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ያለምንም ደም ጠብታ የሥርዓቱን መውደቅ ከሚጠቁም አሟሟት የበለጠ ተመራጭና "አርኪ" አሟሟት አለ ወይ? ለዚህ ይመስላል÷ አበጀ በለው ያለምንም ደም ጠብታ ፊታውራሪን ለመማረክ አቅዶ የተነሳዉና በኋላም በ3 ሰው ሞት ብቻ እጃቸውን ለመያዝ የበቃው፡፡ በዚህም፤ ለተነሳው ጭብጥ የፊታውራሪ አሟሟት አንዳች የሆነ ታላቅ ሚና እንዳለውና አመክንዮአዊም እንደሆነ መገንዘብ አያዳግትም፡፡ ፍካሬያችንን ለማጽናትም÷ በሐያስያኑ ሒስ ላይ ሌላ ማስረጃ እያጠየቁ ("justify" እያደረጉ) እና ሌሎች ዋቢዎችን እየነቀሱ በሙግቱ መግፋት ይቻላል፡፡

ደራሲ ሀዲስ÷ በተለያዩ ጊዜያት "እንደሚባለው" የተንዛዛውን የመጽሐፉን ታሪክ ለመቋጨት ሲባል በድንገት (ከታሪኩ ተጠየቂያዊ ምክንያት የመነጨ ሳይሆን በራሳቸው መርጫ) ፊታውራሪ ከፈረስ ላይ አዘልለው÷ አለት ላይ ፈጥፍጠው እንደገደሏቸው የሚነሳው አስተያየት ተራ አባባል እንጂ አመክንዮአዊ እሳቤ አይደለም ማለት ይቻላል፡፡ ይልቁንም ደራሲው አስበውት÷ የገጸባህርይዉን ግብርና ባህርይ መርምረው የፈጸሙት ግድያ ነው፡፡

መጽሐፉን በጥንቃቄ ላነበበ ሰው (ፍ.እ.መ. ገጽ 252 ላይ) ይበልጥ÷ ደራሲው ስለ ፊታውራሪ አሟሟት ቀድመው የጠቆሙትን ትንቢትም እንበለው ንግር (foreshadowing) መኖሩን ያረጋግጣል፡፡ የፊታውራሪ መሸሻ አባት÷ ፊታውራሪ በሪሁን÷ "... ለተራበ፣ ፍሬያቸውን፡ ለደከመው፡ ጥላቸውን... መውሰድ፡ ብቻ፡ ሳይሆን፡ መስጠት፡ ጭምር፡ የሚያውቁ..." እንደሆኑ በባላገሮች አድማ ላይ የተናገሩት ብላታ ንጉሤ÷ በእርሳቸው ምትክ የተተኩት ፊታውራሪ መሸሻ ግን ጨካኝና አረመኔ እንደሆኑ÷ ወደፊትም ሰውን አጥፍተው በመጨረሻም እራሳቸው እንደሚጠፉ በዚህ መሪር ንግግር አስረድተዋል፤

> "... ያገኘውን፡ ሁሉ፡ የሚፈጅ፡ ርጥብ፡ ከደረቅ፡ ሳይለይ፡ ያገኘውን፡ ሁሉ፡ የሚበላ፡ የቁዋያ፡ እሳት፡ በቦታቸው፡ ተተካ፡፡ እንደምታውቁት፡ **የቁዋያ እሳት፡** ርጥብ፡ ከደረቅ፡ ቡቃያ፡ ከድግ፡ አበባ፡ ከፍሬ፡ ሳይለይ ባንድ ላይ ፈጅቶ፡ **ሁሉንም፡ ባንድ፡ ላይ፡ አመድ፡_አድርጎ፡... ራሱም... አመድ፡ የሚሆን፡ ነው!**" ሲሉ... (አጽንኦቱ፤ የዚህ ሒስ አቅራቢ ነው፡፡)

ፊታውራሪ መሸሻን ያስተማሰለው (represent ያደረገው) "የቋያ እሳት" በዚህ ዐውድ ውስጥ የመስረጉ ኑባሬ÷ በዘመኑ ቋንቋ "አጥፍቶ ጠፊ" ከሚባለው ጋራ የሚቀራረብ ፍች ያለው ይመስላል፤ ሁሉንም ሳይመርጥ አጥፍቶ በመጨረሻ እራሱም ይጠፋልና፡፡ ስለዚህ ይህ ሐቲት በዚህ ቦታ ሆን ተብሎ መቅረቡ÷ ወደ ኋላ ላይ ፊታውራሪ መሸሻ በእልኻቸውና "እንዴት እዋረዳለሁ" በሚል የመንፈስ ስካራቸው ... ጠንብዘውና ጎሊናቸውን ስተው አለት ላይ ተነጥፈው ለሚሞቱበት ሁነት÷ ቅድመ ጥቆማ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል÷ የፊታውራሪ መሸሻ (ያስተማሰሉትን የፊውዳል ሥርዓት እሳቤ ውስጥ በማስገባት) ድንገተኛ አሟሟት÷ ከባህርያቸውና ከግብራቸው በራሱ ጊዜ በኃይል ፈንድቶ÷ ከደራሲውም ግላዊ ስሜት ቁጥጥር ውጭ አፈንግጦ የተከሰተ ነው ማለት ይቻላል- የታሪኩ ሂደት በራሱ የፈጠረው ዓይነት፡፡ ምክንያቱም፤ ሀዲስ ፊታውራሪ መሸሻ የወከሉትን በድንጋይ ካብ የተመሰለ ያረጀ ሥርዓት በቀጥታ ተንዶ ይፍረስ የሚል አቋም የላቸውም ማለት ይቻላልና፡፡ ባይሆን÷ ጥገናዊ ለውጥ ቢመጣ የሚፈልጉ ይመስላሉ፡፡ ይህን ጉዳይ ለማስረገጥም÷ "አፈ ሀዲስ" በሚባለው ገጸ ባህርይ በ**ጉዱ ካሳ** ላይ አድረው÷ "... ይህ፡ ሁሉ፡ ሲሆን፡ ሕንፃው፡ **በሙሉ፡ እንዳይፈርስ፡ እንደገና፡ ተሻሽሎ**፡ ሰውን፡ ከድንጋዩ፡ በተሻለ፡ መልክ፡ የሚያሳዩ፡ የህያዋን አቁዋመ፡ ማኅበር እንዲሠራ፡ ያስፈልጋል..." (ገጽ 122÷ አጽንኦቱ የዚህ አጥኚ ነው) የተናገሩትን ሐሳብ ማጤን ተገቢ ነው፡፡ ስለዚህ÷ ‹የፊታውራሪ አሟሟት በብልኻትና በእቅድ የተፈጸመ ነው› ብሎ መደምደም÷ የፍካሬያችን ሐቲት የሚፈቅደው አመክንዮአዊ ማንጸሪያ ነው ማለት ይቻላል፡፡

### *ሐ. ጉዱ ካሳ÷ እንደ ማንጸሪያ*

*ለመሆኑ÷ ካሳ ዳምጤ÷ ለምን "ጉድ" ተባለ?*

በ*ፍቅር እስከ መቃብር*÷ "የገበሬውንና የፊውዳሉን ሕይወት በደንብ ይገልጣል- የሁለቱን የመደብ ትግል ሳይቀር፡፡ ደበበ አማላይነቱ ያለው እኔ አንዳንድ ጊዜ ጉዱ ካሳ በገሀዱ ሕይወት ውስጥ ይገጥመኛል፡፡ እስከዚህ ድረስ ነው ልቦለዱ ውስጣችንን የነካው" (ዘሪሁን 1982:27) የሚለው÷ የሥነ ጽሑፍ ባለሙያዎቹ ባደረጉት **ውይይት** ላይ የተነሳዉ ሐሳብ÷ ካሳ ዳምጤ ለምን "ጉድ" እንደተባለ ያላጤኑና ገጸባህርይዉ ከኖረበት ዘመን አንጻር ያልተመለከት በነሲብ የተሰነዘረ አስተያየት ይመስላል፡፡

በርግጥ÷ *ፍቅር እስከ መቃብር* ሲነሳ÷ ከአቀንቃኞቹ ገጸባህርያት ውስጥ በተባ ምላሱ የወቅቱን ሥርዓት ሲሸነቁጥ "ጉድ" የተሰኘው ገጸባህርይ፤ "ካሣ ዳምጤ"ን ማንሳት የሚያስፈልግበት አጋጣሚ ብዙ ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ ስለ መጽሐፉ ጭብጥ ለመናገር ሲታሰብ እንኳ የካሳ ዳምጤን በሳል ንግግር መጭመቅ እንደሚያስፈልግ ብዙዎቹ ተመራማሪዎች ማተታቸውን ያስታውሷል (ቴዎድሮስ 2001፤ ብርሀኑ 1992፤ ደበበ 1982፤ Molvaer 1997, Wondwosen 1998, Fikre 1983)፡፡ በዚህ ክፍል ታዲያ አንድ ነጠላ ጉዳይ አንስተን እናስተነትናለን፡፡ እንዲህ በማለት እንጀምር፤ ለመሆኑ÷ **ካሳ ዳምጤ÷ ለምን "ጉድ" ተባለ?**

በቀዳሚነት÷ የካሣ ዳምጤን "ጉድነት" ከመፈከራችን በፊት÷ ከጉድነቱ በትይዩ "ገጸ ክርስቶት" ሰብእና አለው የሚለውን የወንድወሰንን (Wondwosen 1998) ጥናት ባጭሩ ስንቃኝ÷ ጥናቱ÷ በ*ልብ ወለድ ታሪክ* እና በ*ፍቅር እስከ መቃብር* ላይ ስለተሣሉ "ገጸ ክርስቶስ" ገጸ ባህርያት ሲፈትሽ÷ ጉዱ ካሳን አንደኛው ገጸ ክርስቶስ እንደሆነ ለማጠየቅ ማተቱን እናያለን፡፡ ጉዱ ካሣ በክርስቶስ "አምሳል" ተመስሎ መወከሉ ጥያቄ ቢያጭርም ጥናቱ÷ አመክንዮአዊ በሆነ መንገድ ያስተነተነዉና የፈከረዉ ይመስላል፡፡ ጉዱ ካሣ እውነትና ፍቅር፣ ነፃነት፣ ሰላም ያለበት ዓለም እንዲፈጥር በፅናት መታገሉ÷ የሚኖርበትን ሥርዓት መሔሱና አማራጭ የተሻለ ሥርዓት ማመላከቱ÷ ትሕትናውና ለሌሎች ሲል መሰቃየቱ... ለክርስቶሳዊ ማንጸሪያው÷ ግብሩና ባህርይው እንደሆኑ በአጽንኦት ተገልጿል፡፡

እዚህ ላይ ግን በርግጥ ለጉዱ ካሣ ገጸ ክርስቶስነት ለግብሩም ይባል ለባህርይው ማንጸሪያ መሆኑ አልባዛበትም ወይ? የሚል ሙግት ለማንሣት እንገደዳለን፡፡ መጽሐፉን በነቢቡ (ላይ ላዩን) ሲመለከቱት÷ ጉዱ ካሣ ትሑት፣ ደግ፣ ለድኾች የቆመና ርኅሩኅ ሰው ይመስላል፡፡ በርግጥ እነዚህን ባህርያት አያጣም፤ ችግሩ ግን በክርስቶስ እንዲመሰል መሆኑ (represent መደረጉ) ነው፡፡ ከክርስቶስ ዋነኛ ባህርይና ግብር አንዱን እንኳ ብናነሣ "ግራህን ሲመታህ ቀኝህን ስጠው" በሚል ብሂል በቀልን ሲቃወም ነው የሚታወቀው፡፡ በግፍ የሰቀሉትን እንኳ÷ "ሳያውቁ ነውና ... አባት ሆይ ማራቸው ..." ማለቱን መጽሐፉ ይናገራል [በታህታዊ ንባብ ስንፈክር ኃጢአት ለሠራ ገኻነብ ወይም እንጦሮጦስ መዘጋጀቱ÷ የበቀል መግለጫ አይሆንም ወይ? የሚል ሌላ ፍልስፍናዊ እሳቤ ማንሳቱን ትተን...]፡፡

በአንጻሩ ጉዱ ካሣ ግን÷ ማኅበረሰቡ በራሱ መመሪያ ቀይዶት ("constraint" የሚለውን ፅንሰ ሐሳብ ልብ ይሏል)÷ ሲናገር ባለማድመጥ÷ ሲሠራ ሥራዉን እንደ "ጉድ" በመቁጠር ነፃነቱን ገፎ÷ ከመነሻው በቃኝ ብሎ እንደ ሳጥናኤል አብዮት እንዳያስነሣም ሰቅዞ ይዞት እንጂ÷ በቀለኛ ነው፤ ‹ግራውን ለመታው ቀኙን የሚሰጥ ሳይሆን አፍንጫውን የሚል› ዓይነት፡፡ በቀለኝነቱ እራሱ የተንቀለቀለና ከጠላቶቹ ህልፈተ ሕይወት በኋላ ሁሉ የማይበርድ ነው፡፡ ለምሳሌ በፊታውራሪ መሸሻና በጥሩ ዓይነት ቀብር ላይ÷ "… እግዚአብሔር÷ ቀደመኝ እንጂ ዛሬውኑ ሁለቱንም እኔ እገድላቸው ነበር!" (ገጽ 491) ማለቱን ማጤን ብቻ በቂ ነው፡፡ ስለዚህ÷ በክርስቶስ መመሰሉ የተጋነነ ይመስላል፡፡ እዚህ ላይ ታዲያ ለመሆኑ÷ ‹ካሳ ዳምጤ ለምን "ጉድ" ተባለ?› የምትል አንዲት ቅንጣት ጥያቄ ማርቀቅ እና አንዳንድ ጥቃቅን ጉዳዮችን ፈር አሲዞ በ**በይነ ቴክስታዊነት**[9] እያናበቡ መፈከር ይቻላል- ይገባልም፡፡

በሌላ በኩል÷ በባህርይው ለየት በማለቱ ሳቢያ "ጉድ" የተባለለት ካሳ ዳምጤ ለግብሩ መገለጫ የሆነው ምናባዊዉ ስሙ÷ በአሁን ዘመንም ለየት ያለ ሥራ ለሚሠሩ ወይም ከማኅበረሰቡ "ላፈነገጡ" ሕያው ሰዎች መጠሪያ በመሆንም÷ በቅጽል ስምነት አገልግሏል፤ እያገለገለም ነው፡፡ ይህ ደግሞ÷ "ጉዱ ካሣ" ከዛሬው ዘመን ሰው ጋር እንኳ የማይገጥም በሚመስለው ባህርይው የተነሳ በተደራስያን አእምሮ የማይረሳና "ግርምት" ጭምር የሚፈጥር ገጸባህርይ መሆኑን ያመለክታል ማለት ይቻላል፡፡

ካሣ ዳምጤ÷ ለምን "ጉድ" እንደተባለ ደራሲው÷ "… ብቻውን ይናገር አንዳንድ ጊዜም ብቻውን ይስቅ ስለነበር ይህን ያዩ ሰዎች **ጉዱ ካሣ** የሚባል ስም አወጡለት" (አጽንኦቱ የዚህ ሒስ አቅራቢ ነው፤ ገጽ 123) በማለት ገልጸውታል፡፡ የአፄ ዮሐንስ 4ኛን የንግሥና ዘመን በሚያነጽረው÷ በአለቃ ለማ ትውስታ ውስጥ ደግሞ÷ "ካሣማ የዲማ ደብተራ ነው፤ የሽማግሌ ልጅ ነው፡፡ ዛድያ ካሣ ጉዱ ይሉታል፡፡ ጉዱማ የሞጋሳ ስሙ ነው" (2003፡ 89) የሚለው መረጃ÷ ከካሣ ዳምጤ ጋራ የሚያገናኘው ነገር ይኖር ይሆን? ብለን እንድንጠይቅ÷ ሀዲስ አለማየሁ "የጉዱን" ገጸባህርይ የቀረጹት "በዲማው ደብተራ" መነሻነት ይሆን? ብለንም "እንድናጠይቅ" ቀደም ብለው ጥያቄ ያጫሩ፣ የሥነ ጽሑፍና የፎክሎር መምህር እንደነበሩ ይነገራል[10]፡፡

*መንግሥቱ ለማ ላቀናበሩት መጽሐፈ ÷ መግቢያ የጻፉት ሥርግው* (2003፡ xvi) እንደሚሉት ከሆነ÷ "ለእኔ *መጽሐፈ ትዝታ ዘአለቃ ለማ* በይዘቱም በቅርጹም ከ*ፍቅር እስከ መቃብር* ጋር ይመሳሰልብኛል፡፡ ሁለቱም መጻሕፍት …. ሁለት ግለሰቦች ዙሪያ ያጠነጥናሉ፡፡ በበዛብህ ቦጋለና በለማ ኀይሉ፡፡ …. ሁለቱም ለዲማው ጉዱ ካሳ ወዳጆች ናቸው" ማለታቸውን ይዘን÷ መጽሐፉን ከተለያየ አቅጣጫ በመመርመር ጉዱ ካሣ "ጉድ" የሚለው ቅጽል ስም ለምን እንደወጣለት÷ አንድ ትርጓሜ ላይ እንድንደርስ÷ ከዚህ በታች ከመጽሐፉ የተወሰዱ አስረጅዎችን እንጠቅሳለን፡፡ አስረጂዎቹም፡-

1. "ስለዚህ ካሣ ዳምጤ የማህበሩን አሮጌ ስሪት ጠልቶና ነቅፎ፣ አሮጌ ስሪት ባርያ የሆኑትን የማህበሩ አባሎች ንቆና ተፀይፎ በመንፈሳዊውም ሆነ በአለማዊው ስሪትና ህግ ላይ መንፈሱ ሸፍቶ፣ የራሱን አሳብ ለራሱ ካልሆነ የሚያካፍለው ጉዋደኛ የለው፡፡ የሚናገረው ለሌሎች አይጥም ሌሎች የሚናገሩት ለሱ አይጥመው፤ በከበበው አለም ውስጥ የግሉን አለም ፈጥሮ በሰው መሀከል ብቻውን ሆኖ የሚኖር ሰው ነበር፡፡" (ገጽ 123)፣
2. "…. የስዋን ቅንነት፤ የስዋን መልካም ስሜት፤ የስዋን የተዋበ ፊት ሲያይ ማህበሩ ልክ እንደስዋ ልቡን ከፍቶ፤ ፊቱን አብርቶ፤ እጁን ዘርግቶ፤ የተቀበለው ይመስለዋል" (ገጽ 124)፣
3. "አሳቡ ከሰው አሳብ አለመግጠሙ ካልሆነ በትምህርት መቼም እሱን የሚያክል የለም ሲሉ እሰማለሁ ምን ላድርግ?" አሉ ወይዘሮ ጥሩ አይነት … (ገጽ 127)፣

[9] ቴክስቶችን (texts) እርስ በርስ እያጋቡና እያግባቡ ማናበብን ብሎም አንዳች የሆነ ትርጉም ማርቀቅን/መፈከርን፣ "በይነ ቴክስታዊነት" (Intertextuality) ልንለው እንችላለን (Allen 2000)፡፡

[10] ይህን በሚመለከት÷ በኢትዮጵያ ራዲዮ "የመጻሕፍት ዓለም" መርሐ ግብር ላይ የትረካዉን መጠናቀቅ አስመልክቶ÷ ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ ከደጀኔ ጥላሁን ጋራ ሲወያዩ ተመሳሳይ ጉዳይ ማንሳታቸውን÷ በልጅ አእምሯቸው ቢሆንም እንደሚያስታውሱት÷ ቴዎድሮስ ገብሬ (ተ/ፕሮፌሰር) ለተማሪዎቻቸው ተናግረዋል፡፡

4. ... የጉዱ ካሣ እናትና ዘመዶች ምሽት ሊያጋቡት ከባላባት ባላባት ሲያማርጡ እሱ አፈረ ጠላቱን "እንቆጳዝዮን" ብሎ ሰይሞ አገባና እናቱንም ዘመዶቹንም **አሳፈራቸው፡፡** (አጽንኦቱ የዚህ ሒስ አቅራቢ ነው፤ ገጽ 330)፣
5. "ላባትሽና ለናትሽ ገዳያቸው የገዛ ከንቱነታቸው ነው እንጂ አንቺ አይደለሽም፡፡ ስለ በዛብህ ለነገርሽኝ ግን የምሰጠው ስምም መልስም የለኝም፡፡" አለ ጉዱ ካሳ እንባው በግራ ቀኝ ጉንጮቹ እየወረደ፡፡ (ገጽ 551)፣

የሚሉት ናቸው፡፡ እነዚህ ከ1-5 የቀረቡት አስረጂዎች ለናሙና የተመረጡ ፍንጭ ሰጪዎች ናቸው፡፡ እነዚህን በአንድ ላይ ጨምቀን ስንፈክራቸው ወደ አንድ መደምደሚያ ላይ ያደርሱናል ተብሎ ይታሰባል፡፡

ከላይ የቀረቡት አስረጂዎች እንደሚገልጹት፤ ካሣ ዳምጤ የሚኖርበት ሥርዓተ ማኅበር እርሱ ቀደም ብሎ ከኖረበት "ከየዚያን ጊዜዉ" ማኅበር ጋራ የሚግባባና የሚጋባ እንጂ፥ ከእርሱ ንቃተ ኅሊና ጋራ የማይገጥም ኋላቀር ሥርዓተ ማኅበር ነው፡፡ ጉዱ ካሣም፥ አሮጌዉን ሥርዓት በአደባባይ ነቃፊና ጥዩፍ በመሆኑ፥ ሐሳቡን የሚያካፍለው አንድም እንኳ ጓደኛ የሌለው እና በከበበው ዓለምም ውስጥ የግሉን ዓለም ፈጥሮ በሰው መሀከል ብቻውን የሚኖር ጉደኛ ሰው ጭምር ነው፤ በሌላ በኩል፥ ከሰብለ ጋራ ሲጫዋወትና የስዋን የተዋበ ፊት ሲያይ፥ ያ ሥርዓተ ማኅበር ልቡን ከፍቶ የተቀበለው እንደመሰለዉ፥ ግን ደግሞ ማኅበሩ አሽቀንጥሮ እንደተፋዉም ይታወቀል፡፡

በተለይም ካሣ ዳምጤ ራሱ እንደሚያምንበት፥ ከሰው መሀከል ብቻውን የሚኖር ከእርሱ በቀር ሌላ ሰው ያልነበረ መሆኑን፥ መጽሐፉ በግልጽ አቀንቅኖታል፡፡ ጉዱ ካሳ ያመነበትን በግልጽ ለመናገር ወደኋላ የማይል ሐቀኛ ተፈጥሮ እንዳለው፥ በመጨረሻው ሰዓት ላይ እንኳ ሰብለ ስለ ወላጆቿ ሞት የተሰማትን ጸጸት በተሰበረ መንፈስ በትሁትነት ስትነግረው፥ "ላባትሽና ለናትሽ ገዳያቸው የገዛ ከንቱነታቸው ነው እንጂ አንቺ አይደለሽም" የሚለው ኮስታራ ምላሹን ያጤኗል፡፡ ታዲያ ይህን የመሰለ ግለ ሕይወቱን ስንፈትሽ በርግጠኝነት ካሣ ዳምጤ ያለመቼቱ፥ በሐሳብና በአመለካከት ሊቃረበው ከማይችለው ማኅበረሰብ ተለይቶ፥ እርሱ ለብቻው ቀድሞ መፈጠሩን እንረዳለን፡፡

አንድ የሥነ ጽሑፍ ሥራ የሚዳኘው፥ ከድርሰቱ ዘመን አንጻር ቢሆን መልካም ነው[11]፡፡ በመሆኑም እውነት በዚያን ጊዜና ቦታ ላይ እንደ ካሣ ዳምጤ ዓይነት አስተሳሰብ ያለው፥ ከግል ጥቅሙ ይልቅ ለማኅበረሰቡ የሚያስብ፥ ላመነበት ነገር ወደኋላ ሳይል እራሱን አሳልፎ የሚሰጥ፥ እንደሚኖርበት ማኅበረሰብ ሆኖ ሳይሆን እንደግሉ፥ ሰብእናውን ይዞ የሚቆም፥ ወይዘሮ "ጥሩ አይነት"ን የመሰሉ ወግ አጥባቂዎች ከወጡበት ቤተሰብ ወጥቶ እግር አጣቢዉ እንድትሆን "የተሸለማትን ባሪያ" እንስት፥ ስሚን ቀይሮ የሚያገባ ወዘተ.፥ በአጠቃላይ በዚያ መቼት እንደዚያ ያለ የሰላ ምላስና የበሰለ ራሰ ያለው ሰው ይኖራል ብሎ ማሰብ ትንሽ ሳይከብድ ይቀራል? ግን ለዚህም መልስ ይኖረዋል፡፡

ደራሲው ሀዲስ ያን ማኅበረሰብ እስከ መቼቱ በጥንቃቄ ያውቁታል፤ የወጡበትም ማኅበረሰብ ነውና፡፡ ለዚያ ይሆን ይህን የተዋጣለት መጽሐፍ የጻፉት? ታዲያ ከዚህ በጥንቃቄ ከሚያውቁት ማኅበረሰብ ውስጥ አንድ ብቻ "የማያውቁት" ሰው፥ ጉዱ ካሣን የት አመጡት? ያ የሰላ ምላስ፥ የበሰለ ራስስ የማን ይሆን?

---

[11] ይህን አስመልክቶም፥ ዘሪሁን አስፋው (1985)፥ "ያንድ ዘመን ሥነ-ፅሁፍም (ከሚፈፀሙት) ታሪካዊ ክስተቶች ውጭ አይጠናም፤ በአንድ አገር በአንድ በተወሰነ ታሪካዊ ዘመን የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች በስነጽሁፍ እድገትም ሆነ ውድቀት ላይ ተጽዕኖ ማሳደራቸው አይቀርም፡፡ የአንድን ስነጽሁፍ ሁኔታ ይበልጥ ለማወቅና ለመረዳትም የበቀለበትን፣ የኖረበትንና ያለፈበትን ማህበራዊ ታሪክ አበይት መልኮች ማጤን ያስፈልጋል" (ገጽ 35) በማለት ሐሳቡን በአጽንኦት ገልጸዋል፡፡ በርግጥ፥ ቀደም ሲል እንደተጠቆመው፥ የ*ፍቅር እስከ መቃብርን* የተሳካ ልቦለድነት ለመመስከር፥ "... ደበበ አማላይነቱ ያለው እኔ አንዳንድ ጊዜ ጉዱ ካሳ በገሀዱ ሕይወት ውስጥ ይገጥመኛል፡፡ እስከዚህ ድረስ ነው ልቦለዱ ውስጣችንን የነካው" (ዘሪሁን 1982፡27) ማለታቸው፥ ጉዱ ካሣን ከኖረበት ዘመን የሚነጥል፥ ያለ ዐውዱ የቀረበ ማንጻሪያ አይሆንም ወይ? የሚል ጥያቄ የሚያስነሳባቸዉ ይመስላል፡፡

እንደሚታወቀውና በግለ ታሪክ መሐፋቸው *ትዝታ* (1985) እንደሚያወጉን÷ ደራሲው ይህን መጽሐፍ ከመጻፋቸው በፊት÷ በሀገር ውስጥ የሚሰጡትን የተለያዩ የቤተ-ክህነት ትምህርት ዓይነቶች በሚገባ ያጠናቀቁ÷ በአስተማሪነትና በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ የሠሩ÷ በአርበኝነት (በሌላም ምክንያት) ከሀገር ሀገር የተንከራተቱ÷ ከብዙ ዐዋቂ ሰዎች ጋራ ለመገናኘት የበቁ÷ በተለይም ብዙ የሀገር ውስጥና የውጭ መጻሕፍትን ጠንቅቀው ያነበቡ÷ በጥቅሉ **ብዙ የሕይወት ልምድ የቀሰሙ በሳል ደራሲ እንደሆኑ**[12] በብዙዎች ይታመናል (አብነት 2007፤ ሥርግው 2003፤ ቴዎድሮስ 2001፤ ዮናስ 1992፤ ብርሃኑ 1991)፡፡

በዚህ የሕይወት ልምዳቸው የቀሰሙትን አጠቃላይ ዕውቀት ታዲያ÷ ለዚያ እያለ ለማይኖረው÷ ለዚያ ‹በከረፋ ሥርዓትና ባህል ታጅሎ ጭንቅላቱ ለዶለዶመው÷ ለዚያ...› የፊውዳል ማኅበረሰብ መለወጫ÷ ማስተማሪያ ለማዋል አሰቡ፤ ሀዲስ በመጽሐፋቸው ውስጥ በካሣ ዳምጤ ላይ አድረው÷ **ግለሰባዊ ርዕዮታቸውን አቀነቀኑ**[13]፡፡ ለዚያ ሳይሆን ይቀራል÷ አንዳንድ ሐያስያን ጉዱ ካሣን "አፈ-ሀዲስ" የሚሉት፡፡

እንዲህ ከሆነ ታዲያ÷ ካሣ ዳምጤን ለምን "ጉድ" የሚል ቅጽል ስም አወጡለት? እስከ አሁን የተብራሩት ዝርዝር ጉዳዮች የሚያመለክቱት÷ ካሣ ዳምጤ በአስተሳሰቡና በአመለካከቱ ከዚያ ማኅበረሰብ ጋራ በፍፁም የማይመሳሰል መሆኑን ነው፡፡ እንደውም ሥርዓተ ማኅበሩና ካሣ ዳምጤ ሆድና ጀርባ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ገጸባህርይው ያለመቸቱ መፈጠሩ ይመስላል፡፡ በመሆኑም÷ ያ ማኅበረሰብ በሕይወት ልምዱ ጭራሹኑ ዐይቶት የማያውቀውን÷ "ፈላስማ ቦተሊከኛ" እንደ ቶማስ በደመና ተጭኖ በታምር ዱብ ሲልበት÷ "ጉድ" ማለት ይነሰው!? ገጸባህርይው ከተፈጠረበት ማኅበረ ባህላዊ ዐውድ አንጻር ከተዳኘ÷ "ጉድ" መባሉ ተገቢ ነው ማለት እንችላለን፡፡ ደራሲ ሀዲስም ያለ ዘመኑና ያለቦታ በዚያ ማኅበረሰብ አብራክ ፀንሰዉ በድንገት የወለዱት አፈንጋጩ የብዕር ልጃቸውን÷ ካሣ ዳምጤን÷ በጥልቀት የፈተሹትና ታላቁን ሥራቸውን በ"አፈንጋጭነቱ" ጥያቄ እንዳያስነሳባቸው ቀድመው የተረዱት ይመስላሉ፡፡

እንዳይጨነግፉት ደግሞ÷ ያ መታደግን ለሚፈልገዉ ኅብረተሰብ ንቃተ ኅሊናዉ ይለወጥ÷ የትንቢት ርእይም በካሣ ዳምጤ ላይ አድረው ያሳዩት ዘንድ ልባቸው ፈቅዷል፡፡ ሰው እያለ በሌለበት "የጉድ ማኅበር" ውስጥ እንደ ምድረ በዳው መጥምቁ ዮሐንስ ብቻውን እያስጮኹ÷ በአዲስ ርዕዮት ዓለም ማኅበረሰቡን ይጠምቅ ዘንድ ወደዋል- ሀዲስ፡፡ ደራሲው ከገቡበት የከየት አመጣኸው ጥያቄ ምላሽ ይሰጡ ዘንድ÷ ለነዚህ ተፃራሪ እውነታዎች መላ መምታት ነበረባቸው፡፡ በመሆኑም÷ ያለ ጊዜዉና ያለ ቦታዉ የቀረፁት ገጸባህርይ በማፈንገጡ ጥያቄ እንዳያስነሳ÷ "ጉድ" ብለው ሰይመዉ ምናባዊ ፍጥረታቸውንም ለማረቅ÷ ከማኅበረሰቡ የወል ኅሊና ጋርም ለመታረቅ "በዕውቀት ወስነዋል" ብሎ መደምደም የሚቻል ይመስላል፡፡

### ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዓላማ÷ *ፍቅር እስከ መቃብርን* አስመልክቶ በ*ብሌን* (1982) በቀረበው አጠቃላይ ወይይት ላይ ሦስት ጥቃቅን ሁነቶችን ("ስሑት" የሚመስሉ አስተያየቶችን) መዞ በማውጣት÷ ገጸባህርያቱን ማንጸሪያ አድርጎ÷

---

[12] ሀዲስ አለማየሁ በተለይ የ2ኛዉ የዓለም ጦርነት በፈጠረው ጣጣ÷ ቅኝ ገዢዎች ስለሚያደርሱት ስልታዊ በደል፣ ስላበላሹት የትምህርት ሥርዓት እና ያንን ለማስተካከል መወሰድ ስለሚገባው እርምጃ በልቦለዶቻቸው እንደገለጹት ሁሉ÷ በተረቶቻቸውም ተራቀውባቸዋል፡፡ እንደውም ችግሩን በተምሳሌት አግዝፈው በማስረዳት ተረቶቻቸው ብልጫ አላቸው ማለት ይቻላል፡፡ ለዚህ ነው÷ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ በሀዲስ ሥራዎች ውስጥ፣ ***ተረት ተረት የመሰረት*** (1948) በሚል ርዕሥ የቀረበው የተረቶች ስብስብ÷ ከሁሉም የበለጠ ሊመረመር የሚገባ ታላቅ መጽሐፍ ነው የሚለው፡፡ በተለይ÷ ገቢራዊ ሕይወቱ ከተረታዊ ፍልስፍናዉ የማይለይ "ብዙ ኅብረተሰብ" በሚኖርባት ሀገር÷ የሀዲስ ልቦለዳዊ የፈጠራ ተረቶችን በወጉ እያነበቡ አለመወያየት÷ "ብዙ እንደሚያጎልብን" መጠርጠር ብልህነት ነው፡፡

[13] ይህን አስመልክቶ÷ **"ልቦለድ እንደ ርእዮተ ዓለም መገለጫ"** የሚለውን የብርሃኑ (1992) ጥናት ይመለከቷል፡፡ ጥናቱ÷ የሀዲስ አለማየሁን ልቦለድና ኢልቦለድ *ሥራዎቻቸውን* እያወዳደረና እያነጻጸረ መርምሮ÷ ልቦለዶቻቸውን እንደ ርእዮተ ዓለም መገለጫ "Ideological Manifesto" እንደተጠቀሙበት አስተንትኗል፡፡ ሀዲስ ርእዮተ ዓላማቸውን የሚያንፁባቸው 3 "ማህበራዊ አውዶች" ትምህርት ቤት፣ ጋብቻ እና ሽፍትነት እንደሆኑ ጥናቱ አስተንትኗል፡፡ እነዚህን ማኅበረ ተቋማት÷ በኢ-ልቦለድ መሐፎቻቸው ማለትም ***ትምህርትና የተማሪ ቤት ትርጉም*** (1948) እና ***ኢትዮጵያ ምን አይነት አስተዳደር ያስፈልጋታል?*** (1966) ላይ ከገለጹበት ቀጥተኛ አቀራረብ ትይዩ÷ በልቦለድ *ሥራዎቻቸው* (***ፍቅር እስከ መቃብር፣ የልምዣት፣ ወንጀለኛው ዳኛ***) ውስጥም በ3ቱ ማኅበረ ተቋማት ላይ አድረው ርእዮተ ዓለማቸውን በረቀቀ መንገድ እንደገለጹ የተተነተነበት ሥነ ጽሑፋዊ ምርምር መሆኑን እዚህ ላይ ማንሳት ይገባል፡፡

ውስንነት የታየባቸውን የሥነ ጽሑፍ መምህራኑን ምልከታ በሚያርም ደረጃ ለጥያቄዎቹ ምላሽ ማርቀቅ (መፈከር) ነው፡፡ ሒሳዊ ጥናቱ÷ ሦስቱን ገጸባህርያት ማንጸሪያ ያደረጉ ተናጠላዊ ሁነቶች ለመፈከር÷ በዮናስ (1992) ጥናት ላይ ተግባራዊ ከሆኑ የመፈከሪያ ሥልቶች ጋራ÷ የአንባቢ ምላሽ ሒስን አግባብቶና አጋብቶ÷ በፊት ለፊት ከሚነገረን ጀርባ ያለን "ትርጉምና አንድምታ ፈልፍሎ ማውጣት" የሚያስችልን የፍካሬ ሥልት ተጠቅሟል፡፡

ጥናቱ÷ ሰብለ ወንጌልን ማንጸሪያ አድርጎም÷ *ፍቅር እስከ መቃብርን* ለመመርመር ሞክሯል፡፡ የሰብለ ወንጌል ባህርይና ግብር በጥልቀት ሲፈተሽ÷ የባላባታዊው ሥርዓት እጅግ በጠነከረ ሁኔታ እንዳንገፈገፋትና እንደምትጠላው መረዳት ይቻላል፡፡ ሥርዓቱን ብቻም ሳይሆን የሥርዓቱን ትዕምርቶች ጭምር ትጸየፋለች፡፡ የባላባት ልጅ እንድታገባ ብትጠየቅም ዝም ብላ እንደማትቀበለው÷ ይልቁንም እንደምትሟገት÷ ሰብእናዋም በተለምዷዊው ወግ ልማድ የተገራ ብቻ ሳይሆን በተለየ መንገድ÷ በአእምሯዊ ዕውቀት የተቃኘ መሆኑን ይፈክሯል፡፡ ስለዚህ÷ ሰብለ በዛብህን የወደደችው÷ "በፍቅር ጓደኝነት የተቆራኘችው የባላባት ዘር ሲነፈጋት፣ አማራጭ ስታጣ ነው" የሚለው አስተያየት÷ ከሰብለም ሆነ ከልቦለዱ አጠቃላይ ሁኔታ ጋራ የማይሄድ÷ ርዕዮተ ዓለማዊ ወገንተኝነት የታየበት "ስሑት አስተያየት" ነው ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡

የፊታውራሪ መሸሻ አሟሟትም÷ የራሱ የሆነ አንድምታ አለው፡፡ መጽሐፉን ወደ ፊትና ወደኋላ መላልሰው ሳይፈትሹ÷ "በባላገር ተደብድበው ቢገደሉ ነበር የሚያረካ" ይህ ያልሆነው ግን÷ "የደራሲው ምርጫ ስለሆነ ነው" የሚለው ማጠቃለያ÷ አመክንዮኣዊነት የነጠፈበት ውሱን አስተያየት እንደሆነ÷ የአሟሟታቸዉን ምስጢር ለመረዳትም የግል ሰብእናቸውን እንዲሁም ባህርይና ግብራቸውን ማጤን እንደሚገባ÷ ሀዲስም÷ የፊታውራሪ መሸሻን አሟሟት ከዚሁ ግላዊ ባህርያቸው እንዲመነጭ በማድረጋቸው ተሳክቶላቸዋል ማለት እንደሚቻል ጥናቱ÷ አስተንትኗል፡፡

የካሣ ዳምጤን "ጉድ" መባል አስመልክቶም ይህ ጥናት÷ የሐያሲያኑን ውሱን አስተያየት ገርቶ÷ በአዲስ አቅጣጫ ለመፈከር ሞክሯል፡፡ በአስተሳሰቡና በአመለካከቱ ከዚያ ማኅበረሰብ ጋራ በፍፁም የማይመሳሰለው ካሣ ዳምጤ÷ ከሥርዓተ ማኅበሩ ጋራ ሆድና ጀርባ መሆኑን፣ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ÷ ገጸባህርይው ያለመቸቱ በመፈጠሩ÷ ማኅበረሰቡ በሕይወት ልምዱ ጭራሹን ዐይቶት የማያውቀው የተለየና ደፋር ተናጋሪ መሆኑን፣ ደራሲ ሀዲስም ያለ ዘመኑና ያለቦታው በዚያ ማኅበረሰብ አብራክ ውስጥ በድንገት የወለዱት የብዕር ልጃቸውን "አፈንጋጭነቱን" በውል የተገነዘቡ መሆናቸውንና በማፈንገጡ ጥያቄ እንዳያስነሳ "ጉድ" ብለው ለመሰየም መብቃታቸውን ማጠየቅ ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ ግን *ፍቅር እስከ መቃብር* እንዲሁ ላይ ላዩን ብቻ ተነቦ የሚፈከር÷ በተወሰነ ወይም በአንድ ጭብጥ ላይ የሚያተኩር አድርጎ መገመት ስሕተት ላይ ሊጥል እንደሚችል ማስታወስ ተገቢ ነው፡፡ ምክንያቱም÷ በርካታ ሐሳቦች (Ideas)፣ ፍልስፍናዎች፣ ሁነቶች፣... ያሉት መጽሐፍ በመሆኑ፤ እያንዳንዱን ቅንጣት አሀድ በተናጠልና በጥቅል እያነበቡና እየመረመሩ መተንተንና መፈከር የሚጠይቅ÷ የሥነ ጽሑፍ ሐያስያን "የሐሳቦች ልቦለድ" የሚሉት ዓይነት ሥራ ነውና፡፡ ስለዚህ ከላይ እንዳየናቸው ሦስት መጠይቃዊ ማንጸሪያዎች÷ እያንዳንዱ ቅንጣት አሀድ ሁሉ ተጨምቆ ሲፈከር÷ አንዳች የሆነ ጥልቅ እውነትና ውበት እንደሚያሳይ ይህም ሒሳዊ ጽሑፍ ያስረግጣል፡፡

## ማጣቀሻዎች (References)

### አማርኛ


ሀዲስ አለማየሁ፤ 1996፤ *ፍቅር እስከ መቃብር* (10ኛ እትም)፤ አዲስ አበባ÷ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት፡፡

_________፤ 1985፤ *ትዝታ*፤ አዲስ አበባ÷ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

_________፤ 1980፤ *የእልም እዣት*፤ አዲስ አበባ÷ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

_________፤ 1974፤ *ወንጀለኛው ዳኛ*፤ አዲስ አበባ÷ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

_________፤ 1966፤ *ኢትዮጵያ ምን ዓይነት አስተዳደር ያስፈልጋታል?*፤ አዲስ አበባ÷ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

_________፤ 1948፤ *ተረት ተረት የመሰረት*፤ አዲስ አበባ÷ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

______፤ 1948፤ *የትምህርትና የተማሪ ቤት ትርጉም*፤ አዲስ አበባ፦ አርቲስቲክ ማተሚያ
ለማ ኃይሉ (አለቃ)፤ 2003፤ *መጽሐፈ ትዝታ ዘአለቃ ለማ ኃይሉ ወልደ ታሪክ* (*መንግሥቱ ለማ እንደጻፈው፤ ሁለተኛ እትም*)፡፡ አዲስ አበባ፦ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፡፡
*ሥርግው ገላው*፤ 2003፤ "*መግቢያ 1*፤" *መጽሐፈ ትዝታ ዘአለቃ ለማ ኃይሉ ወልደ ታሪክ* (*መንግሥቱ ለማ እንደጻፈው፤ ሁለተኛ እትም*)፡፡ አዲስ አበባ፦ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፤ ገጽ ፫- xvi፡፡
ኅብረት ተዘራ፤ 1993፤ "የሙቼት ገለፃ ሥነ ጽሑፋዊ ፋይዳ በሀዲስ አለማየሁ ልቦለዶች" አ.አ.ዩ.፤ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሁፍ ክፍለ ትምህርት የቀረበ ዲግሪ፡፡

ብርሃኑ ገበየሁ፤ 1991፤ "የገጸባህርያት ስሞች ስነፅሁፋዊ ፋይዳ በአማርኛ ልቦለዶች፤" *የኢትዮጵያ የቋንቋዎችና የሥነ ጽሑፍ መጽሔት* (ቁጥር 9) ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ ገጽ 1-30፡፡
______፤ 1992፤ "ልቦለድ እንደ ርዕዮተ ዓለም መገለጫ፤" *የኢትዮጵያ የቋንቋዎችና የሥነ ጽሑፍ መጽሔት* (ቁጥር 10፤ ልዩ እትም) ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ ገጽ 43-76፡፡
ቴዎድሮስ ገብሬ፤ 2007፤ "የሃያኛው ክፍለ ዘመን የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ማስተማሪያ መጻሕፍት ሁኔታ፤ ታሪካዊ-ሒሳዊ ቅኝት፤" *ብሌን የሥነ ጽሑፍ መጽሔት* (ቅጽ 8 ቁ.1፤ *ታኅሣሥ* 2007)፦ አዲስ አበባ፤ ገጽ 15-48፡፡
______፤ 2001-ሀ፤ *በይነ-ዲሲፕሊናዊ የሥነ ጽሑፍ ንባብ*፤ አዲስ አበባ፦ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፡፡
______፤ 2001-ለ፤ "የዘመን መንፈስ በተመረጡ የአማርኛ ልቦለዶች ውስጥ፤" *መድበለ ጉባኤ* (ደረጀ ገብሬ አርታዒ)፤ አዲስ አበባ፤ የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበር፤ ከገጽ 153-165፡፡
አብነት ስሜ፤ 2007፤ *ፍካሬ ኢትዮጵያ*፤ አዲስ አበባ፡ ፋር ኢስት ትሬዲንግ፡፡
ኤልያስ አያልነህ፤ 1996፤ *የሃዲስ አለማየሁ በ‹ሃያሲያን› እይታ፤ የባችለር፣ የማስትሬትና የዶክትሬት ምርምሮች መዘርዝር ከአህፅሮት ጋር (ከ1964- 1996 ዓ.ም.)*፤ አዲስ አበባ፡ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡
ደስታ ተክለወልድ፤ 1962፤ *ዐዲስ፡ ያማርኛ፡ መዝገበ፡ ቃላት፡፡* አዲስ አበባ፦ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡
ደበበ ሠይፉ፤ 1982፤ "ያማርኛ ልቦለድ እድገት- ከ‹ጦቢያ› እስከ ‹አደፍርስ›፤" (ውይይት)፤ *ብሌን የሥነ ጽሑፍ መጽሔት* (ቅጽ 1 ቁ.1፤ ነሐሴ 1982)፤ አዲስ አበባ፤ ገጽ 19-43፡፡
ይልማ ደምለው፤ 1986፤ "የጉዱ ካሳ፣ የአደፍርስና የካሳሁን ማኅበራዊ ዕይታ፤" አ.አ.ዩ.፤ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሁፍ ክፍለ ትምህርት የቀረበ ዲግሪ፡፡

ዮናስ አድማሱ፤ 1992፤ "‹አስረኛንኩዋ?› ሀዲስ አለማየሁና የማኅበራዊ ሂስ ሥልታቸው፤" *የኢትዮጵያ የቋንቋዎችና የሥነጽሑፍ መጽሔት* (ቁጥር 10፤ ልዩ እትም) ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ ገጽ 77-119፡፡
ዘሪሁን አስፋው፤ 1985፤ "የኢትዮጵያ *ሥነ-ጽሁፍ ሁኔታ* (1950-1985) *አጭር ቅኝት*፤" በነፃ የመጻሕፍት ገቢያ ኮንፈረንስ የቀረበ፤ ግንቦት፣ አዲስ አበባ፡፡
______፤ 1982፤ "ያማርኛ ልቦለድ እድገት- ከ‹ጦቢያ› እስከ ‹አደፍርስ›" (ውይይት)፤ *ብሌን የሥነ ጽሑፍ መጽሔት* (ቅጽ 1፦ ቁ.1፤ ነሐሴ 1982)፤ አዲስ አበባ፦ ገጽ 19-43፡፡
ገዛኸኝ ጸጋው፤ 2010፤ "‹እስከ ማዕዜኑ፣› እንደ ርዕዮተ ዓለም ማቀንቀኛ የ50 ዓመት ግጥም፤" *ባህልን ማወቅና መጠበቅ ለሁለንተናዊ እድገት፤ የአራተኛው አገር አቀፍ የባህል አውደ ጥናት መድበል*፤ ደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ የባህል ማዕከል፤ ገጽ 174-193፡፡
ገዛኸኝ ፀ.፤ 2002-ሀ፤ "የመጀመሪያው የአማርኛ ረጅም ልቦለድ የማን ነው?"፤ *አዲስ አድማስ ጋዜጣ* (ቅጽ 9፣ ቁጥር 516)፤ *ታህሳስ* 3 ቀን 2002 ዓ.ም.፦ አዲስ አበባ፡፡
______፤ 2002-ለ፤ "የሥነ ጽሑፍ ማኅበራዊ ፋይዳ እና የሥነ ጽሑፍ ተመራማሪዎች ትኩረት፤" *አዲስ አድማስ ጋዜጣ* (ቅጽ 9፣ ቁጥር 504፣ ገጽ 18) ጥቅምት 14 ቀን 2002 ዓ.ም.፦ አዲስ አበባ፡፡
______፤ 2001፤ "ገጸ ባህርያት እና ኮከብ ቆጠራ፤" *አዲስ አድማስ ጋዜጣ* (ቅጽ 9፣ ቁጥር 493፤ ገጽ 20) ሐምሌ 4 ቀን 2001 ዓ.ም.፦ አዲስ አበባ፡፡
ፈቃደ አዘዘ፤ 2004፤ "ቁዘማ፣ ባህል እና ልማት በኢትዮጵያ፤" *ልሳነ ኢኮኖሚክስ፡ ርዕይ 2020 በኢትዮጵያ* (*Economic Focus.* VOL.7, NO. 2 June 2004. LISAN Printing Press) ገጽ 1-25፡፡
ፈጠነ ወርቁ፤ 1996፤ "የሰብለ አሳሳል በ‹ፍቅር እስከ መቃብር›፤" አ.አ.ዩ.፤ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት የቀረበ ዲግሪ፡፡

**English**

Allen, Graham. 2000. *Intertextuality*. London: Routledge.
Abrams, M.H. 1999. *A Glossary of Literary Terms*. USA: Heinre and Heine.
Cavallaro, Dani. 2001. *Critical and Cultural Theory: Thematic Variations*. London and New Brunswick, NJ.
Fekade Azeze. 1988. "The Intellectual in the Ethiopian Novel, 1930-1974." Diss. University of Sheffield.
Fikre Tolosa. 1983. "Realism and Amharic Literature." Diss. University of Bremen.
Girma Mengistie. 2002. "Major Symbols in Selected Amharic Novels." A.A.U., M.A. Thesis in Literature.
Kane, Thomas L. 1975. *Ethiopian Literature in Amharic*. Wiesbaden: Otto Harrassowitz.
Molvaer, Redulf. 1997. *Black Lions: The creative Lives of Modern Ethiopian Literary Giants and Pioneers*. Lawrenceville: The Red Sea Press, Inc
Taye Assefa and Shiferaw Bekele. 2000. "The Study of Amharic Literature: An Overview." *Journal of Ethiopian Studies*. Vol. XXXIII, No. 2. Addis Ababa University: Institute of Ethiopian Studies. PP. 27-73.
Wellek, Rene and Austin Warren. 1984. *Theory of Literature*. New Revised Edition. Harcout Brace Jovanovich, Inc.
Wondwosen Adane. 1998. "Incognitos of Christ in the Amharic Novel: A critical study of Archetypcal Mimesis and Its Literary Function Based on Two ‹Novels›" A.A.U. M.A., Thesis in Literatur.
Yonas Admassu. 2001. "On the State of Amharic Literary Scholarship." *Journal of Ethiopian Studies*. Vol. XXXIV No. 1. Addis Ababa University: PP. 25-41.